የሳይንስና ከፍተኛ ትምህርት ሚኒስቴር
Ministry of Science and Higher Education - Ethiopia

በኮቪድ-19 ወረርሽኝ ወቅት የትምህርትና ሥልጠና

ተቋማትና ማኅበረሰብ መተዳደሪያ መመሪያ

መስከረም 2013 ዓ.ም

1. *መግቢያ*

አስተማማኝ የሆነ የኮቪድ-19 ክትባት ወይም ህክምና እስኪገኝ ድረስ ተገቢውን ጥንቃቄ በማድረግ ተዘግተው የነበሩ የትምህርትና ሥልጠና ተቋማትን በመክፈት የተቋረጠውን ትምህርትና ስልጠና እንደገና ማስቀጠል በማስፈለጉ፤

የኢፌዴሪ ህዝብ ተወካዮች ምክር ቤት ጤና ሚኒስቴር ባቀረበው ምክረ ሃሳብ መነሻ ትምህርትና ሥልጠና ተቋማት በቂ ዝግጅት አድርገው ተገቢ ጥንቃቄዎች በመውሰድ፣ ክልከላዎችንና ግዴታዎችን በማክበር እንዲከፈቱ አቅጣጫ በማስቀመጡ

የኢፌዴሪ ህዝብ ተወካዮች ምክር የትምህርትና ተቋማትና ተዋናዮች መከተል ስላለባቸው አሰራርና ግዴታዎችና የሚመለከቱ ዝርዝር ጉዳዮች የሚሸፍኑ መመሪያዎች በሚመለከታቸው አካላት ወጥተው እንዲተገበሩ አመራር በመስጠቱ

ሁሉም የትምህርትና ሥልጠና ተቋማት እና የሚመለከታቸው ባለድርሻ አካላት ተቋማት መልሰው ሲከፈቱ የሚኖሩ ለውጦችን ተገንዝበው የአሰራር ማስተካከያ እንዲያደርጉ ወጥ መመሪያ ማዘጋጀት በማስፈለጉ

የሳይንስና ከፍተኛ ትምህርት ሚኒስቴር በከፍተኛ ትምህርት አዋጅ ቁጥር 1097/2011 መሠረት የሚከተለውን መመሪያ አውጥቷል፡፡

ክፍል አንድ

ጠቅላላ ድንጋጌዎች

አንቀጽ 1፡- አጭር ርእስ

ይህ መመሪያ ''በኮቪድ-19 ወረርሽኝ ወቅት የትምህርትና ሥልጠና ተቋማትና ማኅበረሰብ መተዳደሪያ መመሪያ ……../2013'' ተብሎ ሊጠቀስ ይችላል፡፡

አንቀጽ 2፡- ትርጓሜ

በሌሎች ጸንተው ባሉ የትምህርትና ስልጠና ህጎች ላይ የተሰጡት ትርጓሜዎች እንዳሉ ሆነው ከዚህ በታች ያሉት ቃላት አገባብ ሌላ ትርጉም የሚያሰጣቸው ካልሆነ በስተቀር በዚህ መመሪያ፡-

2.1. "የትምህርትና ሥልጠና ተቋም" ማለት የመንግሥትና የግል የትምህርትና ሥልጠና ተቋማትን ነው፡

2.2. "የትምህርትና ሥልጠና ተቋም ማኅበረሰብ" ማለት በከፍተኛ ትምህርት አዋጅ ቁጥር 1152/2011 አንቀጽ 28ና 34 ከተገለጸው በተጨማሪ ተማሪዎችን እንዲሁም በግቢ ውስጥ የሚገኝን ከተቋሙ ጋር ግንኙነት ያለውን ማንኛውንም ሰው ይጨምራል፡፡

2.3. "የከፍተኛ ትምህርት ተቋማት ማኅበረሰብ አባል" ማለት መምህራን፣ ተማሪዎች፣ የአስተዳደር ሠራተኞች ወይም በግቢ ውስጥ የግንባታና ልዩ ልዩ ፕሮጀክት ሥራ የሚሰሩ፣ በቋሚነት የምግብ አቅርቦት ከውጪ የሚያቀርቡ፣ በግቢ ውስጥ ባሉ ሱቆች፣ ሱፐርማኬቶች፣ ምግብ ቤቶች እና መሰል አገልግሎቶችን የሚሰጡት ሰዎችን ያካትታል፤

2.4. "ተማሪ" ማለት በከፍተኛ የትምህርት ተቋማት በመደበኛ እና መደበኛ ባልሆኑ የትምህርት መርኃ ግብሮች ተመዝግቦ በመማር ወይም አጭር ሥልጠና በመውሰድ ላይ ያለ ነው፡፡

2.5. "ዕጩ ተመራቂ" ማለት ለመመረቅ የሚያስችሉ ሁሉንም ቅድመ ሁኔታዎች አሟልቶ የምረቃ ሥነ-ሥርዓት እስኪከናወንና የትምህርት ማስረጃ ተሰጥቶት እስኪወጣ ያለ ተማሪ ነው፡፡

2.6. "ሥነ ምግባር' ማለት ማንኛውም በተቋሙ ወይም በተቋሙ ማኅበረሰብ አባላት ወይም ከተቋሙ ውጭ ባለ ማኅበረሰብ ላይ አዎንታዊ ወይም አሉታዊ ተጽዕኖ ሊያሳርፍ የሚችል ባህሪይ ሆኖ በማንኛውም ሁኔታ ሊገለጽ የሚችል ነው፡፡

2.7. "የዲሲፕሊን ጥፋት" ማለት በዚህ መመሪያ ወይም በሌሎች አግባብነት ባላቸው ህጐች የተከለከለ ድርጊት መፈፀም ወይም መተባበር ወይም ሲፈጸም እያዩ በቸልተኝነት ማለፍ ነው፡፡

2.8. “የዲስፕሊን *መመሪያ*” ማለት በከፍተኛ ትምህርት አዋጅ 1152/2011 አንቀጽ 86 ንዑስ አንቀጽ 5 *መሠረት* በሳይንስና ከፍተኛ ትምህርት ሚኒስቴር የወጣ የከፍተኛ ትምህርትና ሥልጠና ተቋማት የዲስፕሊን *መመሪያ* ነው፡፡

2.9. “አነስተኛ የዲስፕሊን ጥፋቶች” የሚባሉት ለዲስፕሊን ኮሚቴ ማቅረብ ሳያስፈልግ በዚህ *መመሪያ መሠረት* ኃላፊነት በተሰጠው አካል የምክር፣ የቃል ወይም የጽሑፍ ማስጠንቀቂያ የሚያሰጡ የዲስፕሊን ጥፋቶች ናቸው፡፡

2.10. “ቀላል የዲስፕሊን ጥፋቶች” የሚባሉት ከጽሑፍ ማስጠንቀቂያ እስከ ከባድ የጽሁፍ ማስጠንቀቂያና እንደአስፈላጊነቱ ማህበራዊ አገልግሎት በመስጠት የሚያስቀጡ ዲስፕሊን ጥፋቶች ናቸው፡፡

2.11. “*መ*ካከለኛ የዲስፕሊን ጥፋቶች” ከአንድ ወሰነ ትምህርት እስከ ሁለት ዓመት የሚያስቀጡ (ከትምህር ገበታ የሚያሳግዱ) የዲስፕሊን ጥፋቶች ናቸው፡፡

2.12. “ከፍተኛ የዲስፕሊን ጥፋቶች” የሚባሉት ከሁለት ዓመት እስከ ሶስት ዓመት የሚያስቀጡ (ከትምህርት ገበታ የሚያሳግዱ) የዲስፕሊን ጥፋቶች ናቸው፡፡

2.13. “በጣም ከፍተኛ የዲስፕሊን ጥፋቶች” የሚባሉት ከዩኒቨርሲቲው የትምህርት *መ*ርኃ-ግብር ሙሉ በሙሉ መሰናበትን የሚያስከትሉ የዲስፕሊን ጥፋቶች ናቸው፡፡

2.14. "ኮቪድ-19 ወረርሽኝ" ማለት በዓለም የጤና ድርጅት በዚህ ስም የሚጠራው ተላላፊ በሽታ ነው፤

2.15. “ማስክ” ማለት በጤና ሚኒስቴር ኮቪድ-19 ወረርሽኝን በትክክል ለመከላከል የሚያስችል በፋብሪካ የሚመረት ወይም በቤት ውስጥ የሚዘጋጅ አፍና አፍንጫን ለመሸፈን የሚያገለግል ጭምብል ነው፡፡

2.16. “አካላዊ *መ*ራራቅ’’ ማለት የኮቪድ-19 ወረርሽኝ ከሰው ወደ ሰው የሚኖረውን ስርጭት ለመቀነስ ወይንም ለመግታት በሁለት ወይንም ከዛ በላይ በሆኑ ሰዎች *መ*ካከል ከአንድ አስከ ሁለት ሜትር ርቀትን መጠበቅ ነው፤

2.17. ‘‘ስብሰባ’’ ማለት አራትና ከዚያ በላይ ሆኖ በአንድ ቦታ በአካል *መ*ገኘት ነው፡፡ ነገር ግን በትምህርትና ሥልጠና ተቋማት ውስጥ የመማር ማስተማሩን ሂደት ለማስቀጠል የመነጋገር፣ ሥልጠና የመስጠት፣ የመወያየት፣ ግንዛቤ የማስጨበጥ፣ ተግባራትን አያካትትም፡፡

2.18. “ለይቶ ማቆያ” ማለት የዶርም አገልግሎት ለሚሰጣቸው ተማሪዎች ለኮቪድ 19 በሽታ የተጋለጡ፣ የተጠረጠሩ ወይንም ተመርምረው በበሽታው መያዛቸው ሲረጋገጥ በተቋሙ ግቢ ውስጥ የሚቆዩበት ስፍራ ነው፤

2.19. “የኮቪድ-19 ምልክቶች” ማለት በኮቪድ-19 የተያዘ ሰው ላይ ሊስተዋሉ የሚችሉ እንደ ትኩሳት፣ የራስ ምታት፣ የሳል፣ ጣዕምና ሽታን መለየት አለመቻል፣ የጉሮሮ አካባቢ ቁስለቶችና የመሳሰሉ ምልክቶች ናቸው፤

2.20. “ኮቪድ 19 *ፖ*ዘቲቭ” ማለት በRT PCR ወይም ሌሎች ቫይረሱ በሰውነት ውስጥ መኖሩን ሊያሳዩ በሚችሉ የምርመራ አይነቶች ቫይረሱ የተገኘበት ሰው ማለት ነው፤

2.21. “ቀላል የኮቪድ-19 *ታ*ካሚ” ማለት በኮቪድ-19 የተያዘ ሆኖ የሳንባ ምች በሽታን ወይም ሌሎች የኮቪድ-19 ከፍተኛ ህመም ምልክቶችን የማያሳይ ታካሚ ነው፤

2.22. “*ፀ*ረ ተህዋሲያን ውህድ” ማለት ከኮሮና ቫይረስ *ጋ*ር ንክኪ ይኖርቸዋል ተብሎ የሚታሰቡ እቃዎችን ለማጽዳት የሚውል ከአልኮል ወይም ክሎሪን የተዘጋጀ ውህድ ማለት ነው፤

2.23. “ራስን ማግለል” ማለት የኮቪድ-19 ንክኪ ያለው ወይም ተጠርጣሪ የሆነ ሰው የወረርሽኙን ስርጭት ለመግታት ሲባል ከሌሎች *ጋ*ር ያለውን አካላዊ ግንኙነት በማቆም ራስን ለይቶ ማቆየት ነው፡፡

2.24. “የተቋም *ኃ*ላፊ” ማለት አንድን የትምህርትና ሥልጠና ተቋም በበላይነት የሚመራ ግለሰብ ነው፡፡

2.25. “የተቋም ምክትል *ኃ*ላፊ” ማለት አንድን የትምህርትና ሥልጠና ተቋም በምክትልነት የሚመራ ግለሰብ ነው፡፡

አንቀጽ 3፡- የጾታ አገላለጽ

በዚህ *መመሪያ* ውስጥ የቃሉ አግባብ አስገዳጅ ካልሆነ በስተቀር በወንድ *ፆታ* የተገለፀው የሴትንም *ፆታ* ይጨምራል፡፡

አንቀጽ 4፡- የተፈፃሚነት ወሰን

ይህ *መመሪያ* በመላ ሀገሪቱ በሚገኙ የመንግሥት፣ የግል እና *መ*ንግሥታዊ ያልሆኑ የትምህርትና ሥልጠና ተቋማት ውስጥ ተፈፃሚ ይሆናል::

ክፍል ሁለት
መብቶች፣ የተከለከሉ ተግባራት እና የተጣሉ ግዴታዎች

አንቀጽ 5፡-መብቶች

በሌሎች ጸንተው ባሉ ህጎች የተደነገጉ የትምህርትና ሥልጠና ተቋማት ማህበረሰብ መብቶች እንደተጠበቁ ሆነው በዚህ መመሪያ የተገለጹ ክልከላዎችና ግዴታዎች ተፈጻሚ ይሆናሉ፡፡

አንቀጽ 6፡- የተከለከሉ ተግባራት

6.1. ማንኛውም የትምህርትና ሥልጠና ተቋም የፊት ለፊት ትምህርት መስጠት መጀመር እንደሚችል ከሚመለከተው አካል ቅድመ ሁኔታዎች የተሟሉ ስለመሆኑ ተረጋግጦ ውሳኔ/ፈቃድ ሳይሰጥ እንዲሁም አጠቃላይ የመማር ማስተማር ስራውን በተመለከተ የሚደረጉ የጥንቃቄ እርምጃዎችን ሳያከብር ወይም ሳይከተል ትምህርት መስጠት የተከለከለ ነው፣

6.2. ማንኛውም የትምህርትና ሥልጠና ተቋም ማኅበረሰብ አባል ኮቪድ-19 እንዳለበት እያወቀ ወይም ከለይቶ ማቆያ አምልጦ ወደ ከፍተኛ ትምህርትና ሥልጠና ተቋም ውስጥ መግባት፣ ከተቋሙ ማኅበረሰብ ጋር መቀላቀል ወይም ቫይረሱ ወደ ሌሎች ሰዎች ሊተላለፍ በሚችልበት ሁኔታ ከሌሎች ከትምህርት ተቋማት ማኅበረሰብ አባላት ጋር መገናኘት የተከለከለ ነው፡፡

6.3. ማንኛውም የትምህርትና ሥልጠና ተቋም ማኅበረሰብ አባል እንዲሁም ወደ ተቋሙ አገልገግሎት ለመስጠትም ሆነ ለማግኘት የሚመጣ ሰዉ ለሰላምታም ይሁን ለማንኛውም ዓላማ በእጅ መጨባበጥ፣ ሆነ ብሎ የዕርስ በዕርስ አካላዊ ንክኪ ማድረግ የተከለከለ ነው፡፡

6.4. የአፍና አፍንጫ መሸፈኛ ማስክ ማድረግ፣ ቀሪ መሆኑ እስከሚወሰንበት እና ሥልጣን ባለው አካል በይፋ እስከሚገለጽበት ጊዜ ድረስ ከመኝታ እና ከመመገቢያ ሰዓት ውጪ በማንኛውም ቦታ ማንኛውም ሰው በትምህርትና ሥልጠና ተቋም ውስጥ የአፍና አፍንጫ መሸፈኛ ማስክ ሳያደርግ መንቀሳቀስ በፍጹም የተከለከለ ነው፣

6.5. የትምህርትና ሥልጠና ተቋም ውስጥ ተገልጋዮች በሚቀመጡበት ጊዜም ይሁን በማንኛዉም አኳኋን አገልግሎቱን ሲያገኙ ቢያንስ ከአንድ ሜትር በታች እንዳይጠጋጉ እና የአፍ እና አፍንጫ መሸፈኛ ሳያደርጉ አገልግሎት እንዲያገኙ ማድረግ ወይም በአንድ ጠረጴዛ ከሶስት ተገልጋዮች በላይ እንዲቀመጡ ማድረግ የተከለከለ ነው፣

6.6. የተቀደደ፣ንጽህናዉ ያልተጠበቀና ተገቢ ባልሆነ መልኩ የተደረገ የአፍና የአፍንጫ መሸፈኛ ማስክ ማድረግና መጠቀም የተከለከለ ነው፡፡

6.7. ከተማሪዎች ምግብ ቤት እና ከሌሎች ግቢ ውስጥ ካሉ ምግብ ቤቶች የሚወጡ ትርፍራፊ ምግቦችን ለሌላ ለማንኛውም አካል አሳልፎ መስጠት የተከለከለ ነው፡፡

6.8. ማንኛውም ተማሪ ወይም ሰልጣኝ ተቋሙ ካለበት ከተማ ውጪ የተጓዘ እንደሆነ ቀድሞ የጉዞ ታሪኩን ተቋሙ ውስጥ ላለው ማዕከል ማስመዝገብ ያለበት ሲሆን ከጉዞ መልስ ራሱን በለይቶ ማቆያ ውስጥ ሳያቆይ በቀጥታ ከሌላው ማበህረሰብ ጋር መቀላቀል የተከለከለ ነው፡

6.9. ኮቪድ-19ን ለመከላከል የሚደረጉ የጥንቃቄ መልዕክቶችን ይዘው የተለጠፉት ማስታወቂያዎችን መቅደድ፣ ሌላ ማስታወቂያ ደርቦ መለጠፍ፣ ማበላሸት ወይም በሌላ ቁስ መጋረድ የተከለከለ ነው፡፡

6.10. ማንኛውም የትምህርትና ሥልጠና ተቋም ማኅበረሰብ አባልምንም ዓነት የኮቪድ-19 ምልክቶጭና ስሜቶች ሳይኖሩት ሆነ ብሎ በዉሸት በተቋሙ ላይ ሽብር እንዲነግስ ማድረግ በፍጹም የተከለከለ ነዉ፡

6.11. ማንኛውም የትምህርት ተቋም ማኅበረሰብ አባል አላስፈላጊና በሳይንስ ያልተረጋገጡ የኮቪድ-19 መረጃዎችና አስታያየቶችን በመረጃ መረብም ሆነ በማንኛዉም መልኩ ማሰራጨት የተከለከለ ነዉ፡

6.12. ማንኛዉም ሰዉ ወደ ትምህርትና ስልጠና ተቋማት ሲገባ በር ላይ ባለዉ የሙቀት መለኪያ ሳይለካና ሳያረጋግጥ መግባት የተከለከለ ነዉ፡፡

6.13. የተማሪዎች መዝናኛ፣ ስፖርታዊ ውድድርን በሚመለከት

ሀ. ማንኛውም የአካል ቅርርብንና ንኪኪን የሚፈልጉ የተማሪዎች የቤት ውስጥና ከቤት ውጭ ያሉ መዝናኛዎች፣ የመዝናኛ መሳሪያዎችና ጨዋታዎች በማንኛውም ደረጃ የሚደረግ የቡድን ስፖርት ውድድር ማድረግ የተከለከለ ነው፡፡

ለ. ተማሪዎች በግል ካልሆነ በስተቀር የቡድን ስፖርት መስራት አይፈቀድም፡፡

ሐ. የስነ-ጽሑፍ ምሽቶችና የተለያዩ የመዝናኛ መሰባሰቦች ለኮቪድ-19 ስርጭት ምክንያት ስለሚሆኑ የተከለከሉ ናቸው፡፡

መ. በግቢ ውስጥ ባሉ ላዉንጆችና መዝናኛ ቦታዎች የሚገኙ የቤት ውስጥ መዝናኛ ጨዋታዎች ማድረግ የተከለከሉ ናቸው፡፡

6.14. ማንኛውም የትምህርትና ሥልጠና ተቋም ማኅበረሰብ አባል በግልም ሆነ በቡድን በማንኛውም መልኩ የተቋሙን ሠላማዊ የመማር ማስተማር ሂደት የሚያውክ እንቅስቃሴና ተግባራትን ማቀድ፣ መፈጸም፣ ማስተባበር፣ መተባበር የተከለከለ ነው፡፡

6.15. ማንኛውም የትምህርትና ሥልጠና ተቋም ማኅበረሰብ አባል በግልም ሆነ በቡድን ፖለቲካ፣ ኃይማኖት ወይም ብሔር ተኮር የግጭት መንስኤና አባባሽ የሆኑ፣ አለመግባበትና ጥርጣሬ የሚፈጥሩ እንቅስቃሴዎችና ተግባራትን መፈጸም የተከለከለ ነው፡፡

አንቀጽ 7፡- የተጣሉ ግዴታዎች

7.1. ማንኛውም የትምህርትና ሥልጠና ተቋም ኮቪድ-19 ለመከላከል ትምህርት መስጠት የሚችልበትን አጠቃላይ ሁኔታ የሚደነግግና ከዚህ መመሪያ ጋር የተጣጣመ ማስፈጸሚያ ሰነድ የማዘጋጀት፣ የማስተዋወቅና የማስፈጸም ግዴታ አለበት፡ ፡

7.2. ማንኛውም የትምህርትና ሥልጠና ተቋም ኮቪድ-19 ወረርሽኝን በመከላከል ትምህርትን ለማስቀጠል በየደረጃው የሚያስተባብር ግብረ-ኃይል የማደራጀትና የግንኙነት መሥመር የማዘጋጀትና ለተጠቃሚዎች ምቹ በሆነ መንገድ የማስተዋወቅ ግዴታ አለበት፡፡

7.3. ቢሮዎች፣ ለመማር ማስተማር የሚጠቀምባቸው ክፍሎች፣ ቤተ-መጽሐፍትና ቤተሙከራዎች፣ የተማሪዎች ማደሪያ ክፍሎች በመደበኛነት የሚጸዱና በቂ አየር የሚዘዋወርባቸው እንዲሆኑ የማድረግ ግዴታ አለበት፡፡

7.4. ማንኛውም የትምህርትና ሥልጠና ተቋም በቂ ውሃ፣ ከንክኪ ነጻ የሆኑ የእጅ መታጠቢያዎች፣ ልብስ ማጠቢያዎች፣ ልብስ ማስጫዎች፣ መጸዳጃ ቤቶች የተሟሉ መሆናቸውን የማረጋገጥ ግዴታ አለበት፡፡

7.5. ማንኛውም የትምህርትና ሥልጠና ተቋም በቂ ባለሙያዎች ያሉትና በየደረጃው ህክምና እና መድኃኒት መስጠት የሚችል ክሊኒክ የማዘጋጀት ኃላፊነት አለበት፡፡

7.6. የመኝታና የምግብ አገልግሎት የሚሰጡ የትምህርትና ሥልጠና ተቋማት ተማሪዎችን መልሶ ከመቀበላቸው በፊት በየካምፓሱ እንየሁኔታው የማቆያና የለይቶ ማቆያ (Quarantine and Isolation Center) እና አገልግሎት መስጫ ማዕከል ማዘጋጀት አለባቸው፡፡ ለዚህም ከጤና ተቋማትና ሌሎች ከሚመለከታቸው ተቋማት ጋር በቅንጅት መስራት ይኖርበታል፡፡

7.7. ማንኛውም የትምህርትና ሥልጠና ተቋም ለተማሪዎች/ሠልጣኞቹ፣ ለመምህራኑና ለአስተዳደር ሠራተኞቹ የአፍና አፍንጫ መሸፈኛ ማስክ በተመጣጣኝ ዋጋ ማቅረብ አለበት፡፡

7.8. ኮቪድ-19ን ለመከላከል የሚደረጉ ጥንቃቄዎችን ለሁሉም ተማሪዎች/ሰልጣኞች፣ መምህራንና አስተዳደር ሠራተኞች በቂ ግንዛቤ የመፍጠር፣ በግልጽ በሚታዩ ቦታዎች በቪድዮ ማሳየት፣ በጽሑፍ መለጠፍ አግባብ ባለው መንገድ መልዕክት የማስተላለፍ ግዴታ አለባቸው፡፡

7.9. በቂ፣ የግል መከላከያ ቁሳቁሶችን የሚጠቀሙ እና ግንዛቤ ያላቸው የጽዳት ሠራተኞች እንዲኖሩ የማድረግና በአግባቡ እያጸዱ ስለመሆናቸው የመቆጣጠር ግዴታ አለባቸው፡

7.10. ከኮቪድ-19 ልዩ ባህሪይ አንጻር በቂ የግል መከላከያ (ማስክ፣ ጓንት፣ ቆሻሻ ማጠራቀሚያ ቅርጫት...ወዘተ) ለጽዳት የሚያስፈልጉ ቁሳቁሶችን (ሳሙና፣ ጸረ-ተዋህሳን ኬሚካል/ቴክኖሎጂ...ወዘተ) ቀድሞ የማዘጋጀትና በማይበላሹበት ጊዜና ሁኔታ የማከማቸት) ግዴታ አለበት፡፡

7.11. በቂ የፍሳሽና የደረቅ ቆሻሻ ማስወገጃ ሥርዓትና መሠረተ ልማት የማዘጋጀት ኃላፊነት አለበት፡፡

7.12. የሰው እንቅስቃሴ የሚበዛባቸው አካባቢዎች፣ በብዙ ሰው የሚነካኩ የጋራ መገልገያዎች፣ ጠረጴዛዎች፣ እጀታዎች፣ ቁሳቁሶች ...መሠል ቦታዎችና ዕቃዎች በየቀኑ በሳኒታይዘር ወይም በ70 በመቶ አልኮል የማጽዳት ግዴታ አለበት፡፡

7.13. መማሪያ ክፍሎች፣ የተማሪዎች ማደሪያ፣ ቤተ-ሙከራና ወርክ ሾፖች፣ ቤተ መጽሐፍት፣ ምግብ ቤትና መሰል አካባቢዎች በየቀኑ ቢያንስ ለአንድ ሰዓት ያክል ማናፈስና በተገቢው ማጽጃ ማጽዳት አለባቸው፡፡

7.14. የቆሻሻ ማጠራቀሚያ ቅርጫቶች የያዙት ቆሻሻ ከተደፋ በኋላ ወደ ክፍሎች ከመመለሳቸው በፊት በጸረ-ተዋህሳን ማጽጃ ኬሚካል የጸዱ መሆናቸውን የማረጋገጥ ግዴታ አለበት፡፡

7.15. የእጅ መታጠቢያዎችን ግቢ መግቢያ በር አካባቢ፣ በቢሮዎች፣ በቤተ-መጽሐፍት፣ የተማሪዎች ማደሪያ ህንጻዎች፣ ቤተ-ሙከራ፣ ወርክ ሾፕ፣ ምግብ ቤቶች መግቢያ በሮች አካባቢና ከፍተኛ የሰው እቅስቃሴ በሚገኝባቸው ቦታዎች ላይ ከበቂ ውኃና ሳሙና ወይም ሳኒታይዘር ከተመደቡ ተቆጣጣሪዎች ጋር የማዘጋጀት ግዴታ አለበት፡፡

7.16. ማንኛውም የትምህርትና ሥልጠና ተቋም ማኅበረሰብ አባልና ማንኛውም ወደ ተቋሙ ግቢ የሚገባ ሰው የአፍና የአፍንጫ መሸፈኛ ማስክ ማድረጉን የመቆጣጠር ግዴታ አለበት፡፡

7.17. ማንኛውም በትምህርትና ሥልጠና ተቋም ውስጥ የሚንቀሳቀስ ሰው የሚያደርገው የአፍና የአፍንጫ መሸፈኛ ማስክ ያልተቀደደና ንጽህናው የተጠበቀ መሆኑን የማረጋገጥ ኃላፊነት አለበት፡፡

7.18. በመማሪያ ክፍል የተማሪዎች አቀማመጥ ከመጻፊያ ሰሌዳ እና ከፊት ረድፍ መካከል ቢያንስ አንድ ሜትር ተኩል ርቀት የሚኖረው ሆኖ በተማሪዎች መካከል ብያንስ አንድ ሜትር ርቀት እንዲኖረው መደረግ አለበት፡፡

7.19. በቤተ-ሙከራና በቤተ መጽሐፍት በጠረጴዛ መካከል 1 ሜትር ርቀት መኖሩን እና ተማሪዎቹ ማስክ ማድረጋቸውን ማረጋገጥ አለበት፡፡

7.20. በመመገቢያ አዳራሾች ተማሪዎች እጅ ሲታጠቡ፣ሲሰለፉና ሲመገቡ ተገቢውን ርቀት መጠበቃቸውን ማረጋገጥና ክትትል ማድረግ፡

7.21. አካላዊ ርቀትን የበለጠ ለመጠበቅ መመገቢያ ሰዓትን የማራዘም ፣ ተጨማሪ የማንበቢያ ክፍሎችን የማደራጀት፣ የገጽ ለገጽ ትምህርት ሰዓትን የማሳጠር (40 ደቂቃዎች የማድረግ)፣ ሁሉም ቤተ-መጽሐፍት፣ ቤተ-ሙከራ፣ ምግብ ቤቶች ሥራ ላይ እንዲውሉ መደረጋቸውን እና በሙሉ አቅማቸው አገልግሎት መስጠት መቻለቸውን የማረጋገጥ ግዴታ አለበት፡

7.22. ማንኛውም አካላዊ ቅርርብንና ንክኪን የሚፈጥሩ ስፖርታዊ ውድድሮችና ጫዋታዎች እንዳይካሄዱ የመቆጣጠር ግዴታ አለበት፡፡

7.23. በመግቢያና መውጫ አካባቢ መጨናነቆች እንዳይፈጠሩ አማራጭ የግቢና የህንጻ መግቢያና መውጫ በሮችን ማዘጋጀት አለበት፡፡

7.24. የኮቪድ-19 ተጠርጣሪን የመለየትና የማከም ሥራዎችን በሚመለከት ማንኛውም የከፍተኛ ትምህርት ተቋም፡-

7.24.1. በሁሉም መግቢያዎች የሙቀት መለኪያዎችን በመጠቀም መረጃዎችን የማሰባሰብና ከማስተባበሪያ ግብረ ኃይሉና ከማዕከሉ ጋር በመቀናጀት የክትትል ሥራ የመስራት ግዴታ አለበት፡፡

7.24.2. የማቆያና የለይቶ ማቆያ ማዕከል የማዘጋጀት ተጠርጣሪ ሲገኝም ከሚመለከታቸው የጤና ተቋማት ጋር በመሆን የመከታተል፣ የተሟላ ባለሙያ ያለው ክሊኒክ የማዘጋጀት ግዴታ አለበት፡፡

7.24.3. ማንኛውም የመተንፈሻ አካል ችግር የተከሰተበት ተማሪ ወይም መምህር ወዲያው ተለይቶ ተገቢው ክትትል የሚደረግበት ስርዓት የመዘርጋትና የመቆጣጠር ግዴታ አለበት፡፡

7.24.4. ከሚመለከታቸው የጤና ተቋማት እና ኮቪድ-19 መከላከልና የመቆጣጠር ሥራ ከሚሰሩ አካላት ጋር ፈጣንና መደበኛ የግንኙነት ስርዓት የመፍጠርና ሁል ጊዜ አገልግሎት ላይ ያለ መሆኑን የማረጋገጥ ግዴታ አለበት፡፡

7.24.5. ማንኛውም የትምህርትና ሥልጠና ማኅበረሰብ አባል የሆነ ግለሰብ ኮቪድ-19 ያለበት መሆኑ ሲጠረጠር ወይም በምርመራ ሲረጋገጥ በህክምና ማዕከል ብቻ እንዲገኝ የማድረግና ከሚመለከታው የጤና ተቋማት ጋር በመቀናጀት የመከታተል ግዴታ አለበት፡፡

7.24.6. ከኮቪድ-19 ተጠርጣሪ ወይም ታማሚ ጋር ንኪኪ ያላቸው መምህራንና የአስተዳደር ሠራተኞች በቤታቸው እንዲቆዩ የማድረግና ተማሪዎችን በግቢው ውስጥ ወደተዘጋጀው ለይቶ ማቆያ የማስገባትና ከሚመለከታቸው የጤና ተቋማት ጋር በመቀናጀትና በሰለጠኑ የጤና ባሙያዎች ጋር የመከታተል ግዴታ አለበት፡፡

7.24.7. ማንኛውም የኮቪድ-19 ታማሚ መሆኑ በምርመራ የተረጋገጠ ግለሰብ ከግቢ ውጪ ባሉ የጤና ማዕከላት ብቻ ክትትል እንዲደረግለት የማድረግ ግዴታ አለበት፡፡

7.24.8. ማንኛውም ኮቪድ-19 በሽታ አለብኝ ብሎ እራሱን የሚጠረጥር ወይም በሽታው አለበት ተብሎ የሚጠረጠር የትምህርትና ሥልጠና ተቋም ማኅበረሰብ አባል ሰው ስለመኖሩ የሚያውቅ ማንኛውም የትምህርትና ሥልጠና ተቋማት ማኅበረሰብ አባል በተቋሙ ለዚሁ ዓላማ ተብሎ ለተቋቋመ ማዕከል የማሳወቅ ግዴታ አለበት፡፡ በተመሳሳይ ማንኛውም የትምህርትና ሥልጠና ተቋም ይህንኑ መረጃ ለጤና ሚኒስቴር፣ ለኢትዮጵያ ኅብረተሰብ ጤና ኢንስቲትዩት፣ በአቅራቢያው ለሚገኙ የጤና ተቋም ወይም ባለሞያ በወቅቱ የማሳወቅ ግዴታ አለበት፣

7.24.9. ማንኛውም ወደ የትምህርትና ሥልጠና ተቋም አገልግሎት ለማግኘት የሚመጡ ተገልጋዮች በዚህ መመሪያ መሰረት ቫይረሱን ለመከላከል የሚያስችሉ የንፅህና መጠበቂያ ቁሳሶችን የመጠቀም፣ በአገልግሎት መስጫ ቦታዎች ሁለት የአዋቂ እርምጃ ተራርቀው የመቆም ወይም የመቀመጥ ግዴታ አለባቸው፡፡

7.24.10. ማንኛውም ትምህርትና ሥልጠና ተቋም ተገልጋዮች አንድ ሜትር ተራርቀው የሚቆሙበትን ቦታ ምልክት የማድረግ የመቆጣጠር ኃላፊነት አለበት፣

7.25. ማንኛውም የትምህርትና ሥልጠና ተቋም የትራንስፖርት አገልግሎት ሲሰጥ በህግ ከሚወሰነው የመጫን አቅም ልክ ሰዎችን የመጫን፣ የአፍ እና አፍንጫ መሸፈኛ ላላደረጉ ሰዎችን አገልግሎት አለመስጠት፣ ተሽከርካሪውን ቢያንስ በቀን ሁለት ጊዜ በጸረ-ተዋህሳን ኬሚካል ወይም ቴክኖሎጂ የማጽዳት፣ መስኮቶችን በመክፈት በተሽከርካሪው ውስጥ በቂ የአየር ዝውርውር እንዲኖር የማድረግ እና በዘርፉ በመመሪያ የሚወጡ ሌሎች መወሰድ የሚገባቸውን የጥንቃቄ እርምጃዎች የመተግበር ግዴታ አለበት፡፡

7.26. በትምህርትና ሥልጠና ተቋም ግቢ ውስጥ የሚገኙ የኮንስትራክሽን ፕሮጀክት አሠሪዎች በግንባታ ሳይቶች ላይ አስፈላጊውን ንጽህና ለመጠበቅ የሚረዱ እንደ ውሃ፣ ሳሙና፣ የአፍ እና አፍንጫ መሸፈኛ፣ ሳኒታይዘር ወይንም አልኮል፣ የሙቀት መለኪያ መሳሪያ እንዲሁም የጸረ ተህዋሲያን ግብዓት የማቅረብ ወይንም የማሟላትና የመጠቀም፣ ሰራተኞቻቸው በተቻለ መጠን ርቀታቸው ጠብቀው እንዲሰሩ የማድረግ፣ በግቢ ውስጥ የሚኖራቸውን ለንኪኪ የሚያጋልጡ እቅስቃሴዎችን የመገደብ እንዲሁም በኮንስትራክሽን ዘርፍ የኮቪድ 19 ወረርሽኝ ተጋላጭነትን ለመከላከል፣ ዝግጁነት ለማረጋገጥና ምላሽ አሰጣጥ ሁኔታን በተመለከተ የሚወሰኑ የጥንቃቄ እርምጃዎች የማከበር እና የማስከበር ግዴታዎች አለባቸው፡፡

7.27. ማንኛውም በትምህርትና ሥልጠና ተቋም ውስጥ የምግብ ቤት፣ የሱፐር ማርኬት፣ የሱቅ፣ የፎቶ ኮፒና የጽሕፈት መሣሪያዎች አገልግሎት ላይ የተሰማሩ አካላት በሰራተኞቻቸው እና ተገልጋዮቻቸው መካከል ሁለት የአዋቂ እርምጃ ወይም የሁለት ሜትር ርቀት እንዲኖር የማድረግ፣ የአፍ እና አፍንጫ መሸፈኛ ማድረጋቸውን የመቆጣጠር፣ በሽታውን ለመከላከል የሚያስችሉ አስፈላጊ ነገሮችን የማዘጋጀት፣ ለሰራተኞቻቸው የበሽታውን ስርጭት ለመግታት የሚረዱ የጥንቃቄ ቁሳቁሶችን የማቅረብ፣ በአንድ ጠረጴዛ ከሶስት ሰው በላይ አለማስቀመጥ ሌሎች በአገልግቱ ዘርፉ የሚወጡ መመሪያዎችን የመተግር ግዴታ አለባቸው።

7.28. ማንኛውም የትምህርትና ሥልጠና ተቋም ኮቪድ-19ን ምክኒያት በማድረግ የመማር ማስተማር ሂደቱና ጥራቱ እንዳያስተጓጎል፣በተማሪዎችም ላይ አላስፈላጊ ጫና እንዳይፈጠር የተቋሙ አቅምና ነባራዊ ሁኔታ በፈቀደ መጠን አገልግሎቱን የማመቻቸትና ክትትል የማድረግ ኃላፊነትና ግዴታ
አለበት፡፡

7.29. ማንኛውም ተቋም የመማሪያ፣ የማደሪያ፣ የቤተ-ሙከራ፣ ወርክሾፕ፣ የቤተ-መጽሐፍት፣ የምግብ ቤት፣ የክሊኒክ፣ የለይቶ ማቆያ ማዕከል...ወዘተ ሕንጻዎች ጥገና ኮቪድ-19 የመከላከልና የጥንቃቄ ተግባራትን ታሳቢ በማድረግ ተማሪዎችን ለመቀበል ጥሪ ከማድረጉ በፊት ማጠናቀቅ ይኖርበታል፡

7.30. ማንኛውም ከፍተኛ ትምህርት ተቋም በተረጋገጠና ዕውቅና ባለው ከተዋህሳን ማጽጃ ኬሚካል ወይም ቴክኖሎጂ ግቢውን፣ አገልግሎት መስጫ ማዕከላትንና ማደሪያና መማሪያ ህንጻዎችን፣ ቤተ-ሙከራና ዎርክሾፖችን፣ ሌሎች የጋራ መገልገያ ሕንጻዎችንና ቦታዎችን ተማሪዎች ወደ ተቋሙ ግቢ ከመግባታቸው በፊት የማጽዳት ግዴታ አለበት፡፡

7.31. የተማሪዎች ቅበላ ጥሪ

7.31.1. ማንኛውም ከፍተኛ ትምህርትና ስልጠና ተቋም የተማሪዎች ቅበላ ጥሪ ከማድረጉ በፊት ቅድመ ዝግጅቱን በአግባቡ ስለማጠናቀቁ ከሳይንስና ከፍተኛ ትምህርት ሚኒስቴር ወይም ውክልና ከተሰጠው አካል ፈቃድ ማግኘት አለበት፡፡

7.31.2. ማንኛውም ከፍተኛ ትምህርት ተቋም የተማሪዎች ቅበላ ጥሪ ማድረግ የሚችለው የተማሪዎችን ብዛትና የተቋሙን መሠረተ ልማት ታሳቢ በማድረግ ቢያንስ በሶስት ዙር ነው፡፡ በልዩ ሁኔታ በሳይንስና ከፍተኛ ትምህርት ሚኒስቴር ካልተፈቀደ በስተቀር ሁሉን ተማሪዎች በአንድ ጊዜ መጥራት የተከለከለ ነው፡፡

7.32. የተሟላ መረጃን ተደራሽ ማድረግ

7.32.1. ማንኛውም የከፍተኛ ትምህርት ተቋም ተማሪዎች ኮቪድ-19 ለመከላከል በግቢ ውስጥ ስለሚደረጉ ጥንቃቄዎች በቂ መረጃ እንዲኖረው የተለያዩ የመረጃ መንገዶችን በመጠቀም ተደራሽ ማድረግ ይኖርበታል፡ ፡

7.32.2. እንደተቋሙ ነባራዊ ሁኔታ ለሁሉም ተማሪ በጽሑፍ የተዘጋጀ አጭር ኮቪድ-19ኝን ለመከላከል የሚያስችሉ የጥንቃቄ መልዕክቶችን የየዘ ጽሑፍ በበየነ መረብ እንዲደርስ ማድረግና በየተማሪዎቹ ዶርም ውስጥ በቋሚነት መለጠፍ ይኖርበታል፡፡

7.32.3. በተማሪዎች ጥሪ ወቅት በጉዞና በግቢ ውስጥ በአጠቃላይ ማድረግ ስለሚገባቸው ጥንቃቄዎች በሁሉም የመገናኛ መንገዶች በተለይም በተቋሙ በየነ መረብ ላይ ዝርዝር ጉዳዮችን እንዲያውቁ የማድረግ ግዴታ አለበት፡፡

7.33. የግቢ መግቢያ በር ፍተሻ

7.33.1. ማንኛውም ፈታሽ የእጅ ጓንት፣ የአፍና የአፍንጫ መሸፈኛ ማስክ ማድረግ አለበት፡፡

7.33.2. ተማሪዎች ወደ ግቢ ሲገቡ የያዙትን ሻንጣ በራሳቸው እየከፈቱና በውስጡ ያሉትን ዕቃዎችና አልባሳት በዝርዝር ለሚፈትሽ ሰው እንዲያሳዩ ይደረጋል፡፡

7.33.3. የግድ በፈታሽ እጅ መታየት ያለባቸው ሆኖ ሲገኝ ፈታሽ ግለሰብ ለአንድ ተማሪ ፍተሻ አንድ ጓንት በመጠቀም የሚፈትሽ ይሆናል፡፡

7.33.4. የተማሪ መታወቂያን ማሳየትን በሚመለከት በሪጅስትራርና በትምህርት ክፍል በጋራ የተረጋገጠ የተማሪዎች ስም ዝርዝር መሠረት ተማሪዎች መታወቂያቸው እያሳዩ የሚገቡ ይሆናል፡፡

7.33.5. የማንኛውም ተማሪ መታወቂያውን ለፈታሽ ወይም ለጠየቀው ህጋዊ አካል በግልፅ ማሳየት እንጂ አሳልፎ መስጠት የተከለከለ ነው፡፡

7.33.6. የዲስፕሊን ክስ ወይም ሌላ የተማሪውን መታወቂያ የሚፈልግ ጉዳይ ሲያጋጥም የተማሪውን ሙሉ ስምና መታወቂያ ቁጥር በመጥቀስ የሚፈጸም ይሆናል፡፡

7.33.7. ማንኛውም ሰው ወደ ከፍተኛ ትምህርትና ስልጠና ተቋም ግቢ ሲገባ የሰውነቱ ሙቀት የሚለካ ሲሆን የልኬቱ ውጤት ወደ ጥርጣሬ የሚያመራ ከሆነ ወደለይቶ ማቆያ የሚሄድ ይሆናል፡፡

7.33.8. ማንኛውም ሰው ወደ ከፍተኛ ትምህርትና ስልጠና ተቋም ግቢ ሲገባ ከኮቪድ-19 ነጻ ስለመሆናቸው ተመርምረው የሚመጡትን የምርመራ ሠርቲፊኬት የማጣራት ሥራ የሚሠራ ይሆናል፡፡

7.33.9. ማንኛውም ሰው ወደ ከፍተኛ ትምህርትና ስልጠና ተቋም ግቢ ሲገባ ያልተመረመረ ከሆነ ወደ ለይቶ ማቆያ እንዲገባ የሚደረግ ይሆናል፡፡

7.34. የምዝገባ ዝግጅት

ሀ. ከትምህርት ክፍሎች ጋር የተናበበ በትምህርት ላይ የሚገኙትን የተጣራ የተማሪዎች ዝርዝር ቀድሞ በማዘጋጀት የትምህርት ክፍላቸውን፣ መታወቂያ ቁጥራቸውን፣ የትምህርት ዓመታቸውን፣ ጾታ እና መሰል መረጃዎችን በሚገልጽ መልኩ በማዘጋጀት በበየነ መረብ ለተማሪዎች፣ ለተማሪዎች አገልግሎት፣ ለግቢ ጥበቃና ደህንነት እና ለሚመለከታቸው አካላት እንዲደርስ ያደርጋል፡፡

ለ. በተለያዩ ምክንያቶች በተቋሙ ልመዘገቡና ትምህርት መቀጠል የማይችሉትንና የሌለባቸውን ተማሪዎች ለይቶ ለተማሪዎች አገልግሎት፣ ለግቢ ጥበቃና ደህንነት እና ለሚመለከታቸው አካላት እንዲደርስና ተማሪዎቹም እንዲያውቁት መደረግ አለበት፡፡

ሐ. በተለያየ ምክንያት ውሳኔ ያላገኙና ውጤታቸው ሊያስመዘግባቸው ያልቻሉትን ተማሪዎች ለይቶ የተማሪ ጥሪ ከመደረጉ በፊት በሚመለከተው አካል ውሳኔ እንዲያገኝ በማድረግ ተማሪዎቹም ቀድመው እንዲያውቁት መደረግ አለበት፡፡

መ. የተማሪዎች ወደ ግቢ ከመምጣታቸው በፊት ባሉበት ቦታ ሆነው የተሟላ ምዝገባ ማድረግ እንዲችሉ የሚማሩበትን የኮርስ ዝርዝር የያዘ መመዝገቢያ ፎርማት (Registration Slip) በማዘጋጀት በተቋሙ ድረ ገጽ ላይ መቀመጥ ወይም በበየነ መረብ አማራጮች ለተማሪዎች እንዲደርስ መደረግ አለበት፡፡

ሠ. የሪጅስትራሩ አጠቃላይ አሠራሮች በእጅ የሚቀባበል የወረቀት አሠራርን ያስወገደ ወይም የቀነሰ መሆን አለበት፡፡

7.35. ምዝገባ

ሀ. የተማሪዎች ምዝገባ በበየነ መረብ መካሄድ አለበት፡፡

ለ. የተደራጀ የተማሪዎች ምዝገባ ማካሄጃ ቴክኖሎጂ የሌላቸው ተቋማት ወይም ለመጠቀም የሚቸገሩ ተማሪዎች ቢኖሩ በተለያዩ የበየነ መረብ መገናኛ (ኢ-ሜይል፣ ቴልግራም፣ ፌስ ቡክ፣ ዋትስ አፕ...ወዘተ) አማራጮች በመጠቀም በተጣራው የስም ዝርዝር መሠረት የምዝገባ ፎርሙን በመሙላት እንዲመዘገቡ መደረግ አለበት፡፡

ሐ. ተማሪዎቹም ሲመዘገቡ ስማቸው በተጣራው ዝርዝር መሠረት መመዝገብ በሚችሉ ተማሪዎች ዝርዝር ውስጥ መኖሩን በማረጋገጥ ወደ ግቢ ከመምጣታቸው በፊት መመዝገብ አለባቸው፡፡

7.36. *መታወቂያ*

ሀ. የመታወቂያ ዕድሳትም ሆነ ቅያሪ አገልግሎት የሚሰጠው ተጠሪቶ ምዝጋባ ላካሄዱ ተማሪዎች ብቻ ይሆናል፡፡

ለ. ዲጂታል መታወቂያ ያላቸው ተቋማት የመታወቂያ ዕድሳትን በተጣራው የተማሪዎች ዝርዝር መሠረት በአንድ ማዕከል በአካል መምጣት ሳያስፈልግ ያለ ንኪኪ ማደስ አለባቸው፡፡

ሐ. የመታወቂያ ደብተር የሚጠቀሙ ተቋማት አላስፈላጊ የተማሪዎች ሰልፍ መጨናነቅን ለመቀነስ የመታወቂያ ዕድሳት ወይም አዲስ መታወቂያ ዕድላ ተማሪዎቹ በሚገኙበት ትምህር ክፍል መሆን አለበት፡፡

መ. መታወቂያ የጠፋበት ተማሪ ሲያመለክት ለአንድ ጊዜ ብቻ በትምህር ክፍል ኃላፊ ተማሪው በትምህርት ክፍሉ ውስጥ ሲማር የነበረና አሁንም መቀጠል የሚችል መሆኑን ሲያረጋግጥ በትምህርት ክፍሉ በኩል የሚሰጥ ይሆናል፡፡ በድጋሚ ሲጠየቅ ግን መደበኛውን የመታወቂያ ዕድሳት ሂደት የሚከተል ይሆናል፡፡

7.37. የትምህርትና ስልጠና ተቋማት በዕቅድ የሚመራ ግብረ ኃይል በማደራጀት የተጠናከረ የአዕምሮ-ጤና፣ የስነ-ልቦና እና ማህበራዊ የምክር አገልግሎትና ድጋፍ (Mental Health and Psycho-social Support) ለተቋማቱ ተማሪዎች፣ መምህራን አስተዳደር ሠራተኞች እና የተለያዩ ሚዲዎችን በመጠቀም ለተማሪዎች ቤተሰብ የመስጠት ግዴታ አለባቸው፡፡

ክፍል ሶስት
መማር ማስተማርና ምዘና

አንቀጽ 8፡- *መማር ማስተማር (የኮርስ ድልድል፣ የማስተማሪያ ግብዓቶች ዝግጅትና የትምህርት አሰጣጥ)*

8.ነ. ማንኛውም የትምህርትና ስልጠና ተቋም ኮቪድ-19 የመከላከል ቅድመ ሁኔታዎችንና ልዩ የመማር ማስተማር ፕሮግራምን ታሳቢ ባደረገ መልኩ ተማሪዎችን ከመጥራቱ በፊት ፡

ሀ. በአንድ ጊዜ የተማሪ መምህር ግንኙነት ከ40 ደቂቃዎች ባልበለጠ ሆኖ የተሻሻለ የአካዳሚክ ካሌንደር ማዘጋጀት አለበት፡፡

ለ. መምህራን የሚያስተምሩትን የትምህርት ዓይነትና የመማሪያ ክፍል ድልድል በማድረግ ፕሮግራሙን ለተማሪዎችና ለመምህራኑ ማሳወቅ አለበት፡፡

ሐ. እያንዳንዱ መምህር ለሚያስተምረው ትምህርት ዝርዝር ኮርስ አውትላይን እና የምዘና ዓይቶችንና ጊዜያትን በማካተት ተዘጋጅቶ ለተማሪዎች በበየነ መረብ እንዲደርስ ማድረግ አለበት፡፡

8.2. የትምህርት አሰጣጡ በኮርስ በድልድሉ መሠረት እያንዳንዱ የተማሪዎችን እርስ በእርስና ከመምህሩ ጋር የአካል ግንኙነትን በሚቀንስ መልኩ፡-

ሀ. የኮርስ አሰጣጡ በገጽ ለገጽ፣ መምህራን በቴክኖሎጂ አማራጭ በርቀት በሚያደርጉት ድጋፍ ወይም ተማሪዎቹ በግላቸው በማንበብ በሚማሩበት አማራጮች የሚሰጥ ይሆናል፡፡ ከእነዚህ ሶስት አማራጮች ውስጥ እንደኮርሶቹ ጠባይ በትምህርት ክፍሉ ይወሰናል፡፡ አፈጻጸሙንም ዲኑ የመከታተል ኃላፊነት አለበት፡፡

ለ. የኮርሱ ልዩ ባህሪይ አስገዳጅ ካልሆነ በስተቀር በቴክኖሎጂ አማራጭ በርቀት የሚደረጉ ወይም ተማሪዎቹ በግላቸው በማንበብ የሚማሩበት አማራጮች ከገጽ ለገጽ አማራጭ ቅድሚያ ሊሰጣቸቸው ይገባል፡፡

ሐ. እያንዳንዱ የኮርስ መምህር ለተመደበበት ኮርስ የማስተማሪያ ሞጁሎችን፣ ማጣቀሻና አጋዥ መጽሐፍትን በሶፍት ኮፒ በጥራት በማዘጋጀት ለተማሪዎች ተደራሽ ማድረግ ይኖርበታል፡፡

መ. የኮርስ መምህሩ የሶፍት ኮፒ ማንበቢያ መሣሪያዎች የሌላቸው ተማሪዎችን እየለየ ተገቢውን ጥንቃቄ በማድረግ በሃርድ ኮፒ ተደራሽ የማድረግ ኃላፊነት አለበት፡፡

ሠ. ማንኛውም መምህር በቀን ስምንት ሰዓት የመስራት ግዴታውን መወጣት አለበት፡፡

8.3. መማሪያ ክፍልና የማስተማሪያ መሣሪያዎች አጠቃቀም

ሀ. ትምህርት ክፍሉ ያሉትን የመማሪያ ክፍሎች ለገጽ ለገጽ ትምህርት ሲደለድል አንድ ክፍለ ጊዜና ቀጣይ ክፍለ ጊዜ መካከል የማጽዳና የማናፋስ ሥራ የሚሰራበት ቢያንስ የአንድ ሰዓት ክፍተት እንዲኖር ማድረግ አለበት፡፡

ለ. የመማሪያ ክፍል ወንበር አቀማመጥ

i. ለመምህሩ መንቀሳቀሻ የሚሆን ከመጻፊያ ሰሌዳና ከፊት ረድፍ በሚቀመጡ ተማሪዎች መካካል ቢንስ የሶስት ሜትር ርቀት መኖር አለበት፡፡

ii. የተማሪዎቹ የወንበር አቀማመጥ 2 ሜትር አካላዊ ርቀት የጠበቀ መሆን አለበት፡፡

ሐ. የመማሪያ ክፍሎች በርና መስኮት በመማር ማስተማር ወቅት ሁል ጊዜ ክፍት መሆን አለባቸው፡፡ መምህሩም በቂ የአየር ዝውውር መኖሩን ሳያረጋግጥ ማስተማር የለበትም፡፡

መ. ማንኛውም ወደመማሪያ ክፍል የሚገባ መምህርና ተማሪ ከመግባቱ በፊት እጁን በሳሙና በአግባቡ በተዘጋጀው መታጠቢያ ቦታ መታጠብና በመማሪያ ክፍል ውስጥም አፍና አፍንጫውን በማስክ የመሸፈን ግዴታ አለበት፡፡

ሠ. በመማሪያ ክፍል ውስጥ ምንም ዓይነት አካላዊ ቅርርብ እንዲኖር የሚያደርግ የቡድን ውይይት የተከለከለ ነው፡፡

ረ. ማንኛውንም ተንቀሳቃሽ የማስተማሪያ መሣሪያ (ኤል ሲዲ፣ ፖይንተር፣ ዳስተር፣ ኮምፕዩተር...ወዘተ) በጸረ-ተዋህሳን ወይም በሌላ ቴክኖሎጂ ሳይጸዳ በእጅ መቀባበል የተከለከለ ነው፡፡

ሰ. በመማሪያ ክፍል ተገጥመው የሚገኙ ማንኛውንም የማስተማሪያ መሣሪያዎችን (ስማርት ቦርድ፣ ኤል ሲዲ፣ ...የመሳሰሉትን) ከተፈቀደለት ሰው በስተቀር ማጽዳትም ሆነ መነካካት ክልክል ነው፡፡

ሸ. የመማሪያ ክፍሎችን መዝጋትና መክፈት ለዚሁ በተቋሙ በተመደቡ ሠራተኞች ብቻ የሚከናወን መሆን አለበት፡፡ የግዴታ ሲሆን የእጅ ጓንት በማደድረግና ኬሚካ ማጽጃ በመጠቀም መዝጋትና መክፈት ይቻላል፡፡

8.4. ቤተ-ሙከራና ወርክሾፕ

ሀ. ማንኛውም ተቋም ቤተ-ሙከራና ወርክሾፖችን ህንጻውንና መሣሪያዎቹን አካላዊ ርቀትን ለመጠበቅ በሚመች መልኩ ማደራጀትና የጸረ-ተዋህሳን ኬሚካልን ወይም ቴክኖሎጂን በመጠቀም ተማሪዎችን ከመጥራቱ በፊት ማጽዳት ይጠበቅበታል፡፡

ለ. ቤተ-ሙከራና ወርክሾፕ ለሚጠሩ ተማሪዎች በቂ ይሆን ዘንድ እንደአስፈላጊነቱ ተንቀሳቃሽ የሆኑ ተጨማሪ ቤተ-ሙከራዎችና ወርክሾፖች እንዲያዘጋጁ ይገባል፡፡

ሐ. ማንኛውም የቤተ ሙከራ ወይ የወርክ ሾፕ ትምህርት የጋራ ዕቃዎች ላይ የሚኖረውን ንኪኪ ለመቀነስ የቤተ-ሙከራና የወርክ ሾፕ ትምህርቶች በ"Simulation" በመታገዝ ለሚሰጡ ትምህርች ቅድሚያ መስጠት አለበት፡፡

መ. ማንኛውም ከአንድ ተቋም ወደ ሌላ ተቋም ለቤተ-ሙከራ ወይም ለወርክሾፕ ወይም ለሥራ ላይ ልምምድ የሚደረግ ጉዞ የተከለከለ ነው፡፡

ሠ. ከአንድ የቤተ-ሙከራ ወይም ወርክ ሾፕ ትምህርት ክፍለ ጊዜና በቀጣይ ክፍለ ጊዜ መካከል በተቋሙ በተመደበ አካል የሚከናወን ቢያንስ የአንድ ሰዓት የጽዳትና የማናፈሻ ጊዜ መኖር አለበት፡፡

ረ. የቤተ-ሙከራው ወይም የወርክ ሾፑ ልዩ ባህሪይ ካላስገደደ በስተቀር ሁሉም ቤተ ሙከራና ወርክ ሾፕ በቂ የአየር ዝውውር እንዲኖረው መደረግ አለበት፡፡

8.5. ቤተ-መጽሐፍት

ሀ. ማንኛውም ሰው ወደ ቤተመጽሐፍት ሲገባ እጁን በሳሙና በአግባቡ መታጠብና ቤተ መጽሐፍት ውስጥ ሁል ጊዜ አፍና አፍንጫ መሸፈኛ ማስክ ማድረግ አለበት፡፡

ለ. ማንኛውም ከፍተኛ ትምህርት ተቋም የቤተ-መጽሐፍት አቀማመጥ አካላዊ ርቀትን የጠበቀ፣ ተማሪዎች ፊት ለፊት የማይቀመጡበት (ጀርባ ለጀርባ የሚቀመጡበት)፣ “እዚህ ይቀመጡ”ና “እዚህ አይቀመጡ” የሚል ምልክቶች የተደረገበት መሆን አለበት

ሐ. ቤተመጽፍት በቀን ቢያንስ ሶስት ጊዜ መጽዳት ያለበት ሲሆን በተለይም ጠረጴዛዎቹ በጸረ-ተዋህሳን ኬሚካል መጽዳት አለባቸው፡፡

መ. ቤተ መጽፍት ውስጥ ክፍት ቦታዎችን ስፋት መጨመርና ሁል ጊዜ በቂ የአየር ዝውውር እንዲኖረው መደረግ አለበት፡፡

ሠ. ሁሉም ተቋማት በቤተመጽሐፍት ውስጥ መጨናነቅን ለመቀነስ ሁሉም ቤተ መጽሐፍት አገልግሎት እንዲሰጡ መደረግና ተጨማሪ አስፈላጊው ቁጥጥር የሚደረግባቸው አማራጭ የማንበብያ ቦታዎችን ማዘጋጀት አለባቸው፡ ፡

ረ. ሰርኩሌሽን አካባቢ ያለውን መጨናነቅ ለመቀነስ መጽሐፍትን በሶፍት ኮፒ ለተማሪዎች ተደራሽ እንዲሆኑ ማድረግና ልዩ የረዥም ጊዜ የመጽፍት ውሰት ስርዓት ተዘጋጅቶ መተግበር አለበት፡፡

አንቀጽ 9፡- የምዘና ስርዓት፣ ግብረ-መልስና የውጤት አሰጣጥ

9.1. የተከታታይ ምዘናና ግብረ መልስ በእጅ የሚደረገውን የወረቀት ቅብብሎሽ በሚቀንስ መልኩ በኢ-ሜይል ወይም በሌላ የቴክኖሎጂ አማራጭ በመጠቀም እንዲከናወን መደረግ አለበት፡፡

9.2. ምዘና ለማከናወንና ለማስተዳደር የሚያግዝ ቴክኖሎጂ አማራጭ በተቋም ተዘጋጅቶ ለተጠቃሚዎች መድረስ አለበት፡፡

9.3. የተማሪዎች የመመረቂያ ጽሑፍ መረጃ ለመሰብሰብ ካለው ሁኔታ አንጻር ተጋላጭነትን ስለምጨምርና ከፍተኛ የጊዜ እጥረት ስለሚያጋጥም እያንዳንዱ ተቋም በሴኔት ጉዳዩን እንድገመግምና እንዲወስን መደረግ አለበት፡፡

9.4. የወቅቱን ነባራዊ ሁኔታ የትምህርት ጊዜውንና አሰጣጡን ያዛባው በመሆኑ የቀድሞውን ልዩ የተማሪዎች ምዘና ውጤት አሰጣጥ ስርዓት ወጥቶ በሴኔት ጸድቆ ተግባራዊ መደረግ አለበት፡፡

ክፍል አራት
የተማሪዎች አገልግሎት

አንቀጽ 10፡- የተማሪዎች አገልግሎት

10.1. የተማሪዎች ምግብ ቤት

ሀ. የመግብ ቤት ሰልፍ ተማሪዎች ርቀታቸውን ጠብቀው የሚሰለፉበት በየሁለት ሜትሩ የተደረገ ምልክት መኖር አለበት፡፡

ለ. በምግብ ቤት ሰልፍ ላይ መጨናነቅ ለመቀነስ ሁሉም ምግብ ቤቶች በሙሉ አቅማቸው አገልግሎት እንዲሰጡ ማደረግ አለበት፡፡

ሐ. ምግብ ቤት ቢያንስ በቀን ሁለት ጊዜ መጽዳትና በቂ አየር ዝውውር እዲኖረው መደረግ አለበት፡፡ የምግብ ቤት ጠረጴዛ በሳኒታይዘር ወይም በ70 በሙቶ አልኮል መጽዳት አለበት፡፡

መ. የምግብ ቤት አገልግሎት መስጫ ሰዓት

i. ቁርስ 12፡30 – 2፡30 ሰዓት፣

ii. ምሳ 5፡30 – 7፡30 ሰዓት እና

iii. እራት 10፡30 – 1፡00 ሰዓት እንዲሆን ይመከራል፡፡

ሠ. የካፌ ቲከሮችና ስነ-ስርዓት አስከባሪዎች አገልግሎት ሲሰጡ ለአንድ የምግብ ክፍለ ጊዜ አንድ የእጅ ጓንትና የፊትና የአፍ መሻፈኛ ማስክ መጠቀም አለባቸው፡፡

ረ. የእጅ ንኪኪን ለመቀነስ ሲባል ተማሪዎች የምግብ መመገቢያ ካርዳቸውን ለካፌ ቲከሮችና ስነ-ስርዓት አስከባሪዎች በግልጽ ማሳየት እንጂ አሳልፈው መስጠት የለባቸውም፡፡ ለዚህም በየቀኑ ፕሪንት የሚደረግ የተማሪ መለያ ቁጥርን በመጠቀም የቁጥጥር ሥራዉን ማከናወን ይቻላል፡

ሰ. የተማሪዎች ምግብ ቤት የወንበር አቀማመጥ አካላዊ ርቀትን ለመጠበቅ የሚያስችልና አንዱ ተማሪ ለሌላው ተማሪ ጀርባውን ሰጥቶ የሚቀመጠበት ሆኖ መደራጀት አለበት፡

ሸ. በአንድ የምግብ ሰዓት ለአንድ ተማሪ አንድ የምግብ መብያ ሳህን/ትሪ፣ የውሃ/ሻይ መጠጫ ኩባያ፣ ማንኪያ/ሹካ እንዲሆን መደረግ አለበት፡፡ በአንድ የምግብ ሰዓት ምግብ መብያ ቁሳቁሶችን አጥቦ መልሶ መጠቀም የተከለከለ ነው፡፡

ቀ. የምግብ አዘጋጆች፣ አቅራቢዎች፣ አስተናጋጆች እና ምግብ ቤት ጽት ሠራተኞች አገልግሎት በሚሰጡበት ጊዜ ሁሉ የእጅ ጓንት የማድረግ፣ የአፍና የአፍንጫ መሸፈኛ ማስክ የማድረግና ጸጉር መሸፈኛ የማድረግ ግዴታ አለባቸው፡፡ ይንንም የሚቆጣጠር በተቋሙ የተመደበ አካል መኖር አለበት፡፡

በ. የምግብ ግብዓት አቅራቢዎች ኮቪድ-19 ለመከላከል የሚደረጉ ጥንቃቄዎችን የመተግበር ግዴታ አለባቸው፡፡

ተ. ምግብ ቤቶች የምግብ ግብዓቶች የማይበላሹበትን ጊዜን ሁኔታ ታሳቢ በማድረግ ቀድሞ በበቂ መጠን ማከማቸት ይጠበቅባቸዋል፡፡

ቸ. ከምግብ ቤት ምግብ ማውጣት የተከለከለ ነው፡፡

ኀ. ከአንድ የምግብ ክፍለ ጊዜ በኃላ የምግብ ማዘጋጃና ማቅረቢያ ዕቃዎች በጸረ-ተዋህሳን ኬሚካል በአግባቡ መጽዳት አለባቸው፡፡

10.2. የተማሪዎች ክሊኒክ

ሀ. ለደረጃው የሚሆን በቂ ባለሙያ፣ መድኃኒት እና የህክምና መስጫ መሳሪያዎች ያለውና አገልግሎት መስጠት የሚችል ክልኒክ መደራጀት አለበት፡፡

ለ. በጤና ሚኒስቴር የወጡ በጤና ተቋማት ለኮቪድ-19 መከላከል የሚደረጉ ጥንቃቄዎች መተግበራቸውን ተቋሙ ያጋግጣል፡፡

ሐ. በየዕለቱ የታከሙ ተማሪዎችን የተሟላ መረጃ ሚመለከታቸው ያቀርባል፡፡ መረጃዎቹም ከኮቪድ-19 አንጻር የሚተነተኑ ይሆናል፡፡

መ. ማንኛውም የኮቪድ-19 ምልክት የታየበት ታካሚ ሲኖር ወዲያውኑ ለሚመለከታቸው በማሳወቅ ክትትል እንዲደረግ ያደርጋል፡፡

ሠ. ታካሚዎች ርቀታቸውን ጠብቀው እንዲታከሙ ያደርጋል፡፡

10.3. የተማሪዎች የዶርም ምደባና አኗኗር

ሀ. የዶርም ምደባ ህብረ-ብሔራዊ ሆኖ አስቀድሞ ተማሪው ከመጠራቱ በፊት ተጠናቆ ተማሪዎቹም በበየነ መረብ እንዲያውቁ መደረግ አለበት፡፡

ለ. የተማሪዎች የዶርም ቁልፍ ርክክብ የእጅ ንኪኪ በማይኖርበት ሁኔታ መፈጸም አለበት፡

ሐ. በዶርም ውስጥ መደረግ ያለባቸው ጥንቃቄዎች

i. ማንኛውም ጠረጴዛ በዶርም ውስጥ ማስቀመጥ የተከለከለ ነው፡፡

ii. ተማሪዎች ወደ ዶርም ሲገቡ ወጪ የተጠቀሙትን ጫማቸውን ከዶርም ውጪ ማጽዳት አለባቸው፡፡

iii. ተማሪው የሚያድርበትን ዶርም በየቀኑ ማጽዳትና ክፍት አድርጎ ማናፈስ አለበት፡
iv. በአንድ ዶርም ቢበዛ ከዶርሙ የማስተናገድ አቅም 1/3ኛ ተማሪ ብዛት መመደብ አለበት፡፡
v. በማንኛውም አስገዳጅ ሁኔታ አንድ ዶርም ማስተናገድ ከሚችለው 50 በመቶ በላይ የተማሪ ብዛት መመደብ በጥብቅ የተከለከለ ነው፡፡

መ. ማንኛውም ተማሪ በማንኛውም ጊዜና ሁኔታ የራሱ ወዳልሆነ ዶርም መግባት በጥብቅ የተከለከለ ነው፡፡

ሠ. ማንኛውም ተማሪ መጀመሪያ ከተመደበበት ዶርም ወደሌላ ዶርም ማዛወር አይቻልም፤ ሆኖም በህመም ወይም ልዩ ድጋፍ የሚያስፈልግ ሆኖ ሲገኝ በተማሪዎች አገልግሎት ዳይክተር ተጠይቆ በዘርፉን በሚመራ ምክትል ፕሬዚዳንት ሲጸድቅ ማዛወር ይቻላል፡

ረ. ማንኛውም ተማሪ የተጠቀመበትን መጸዳጃና ሻወር ቤት ማጽዳት አለበት፡፡

ሰ. የመኖሪያ ህንጻ ኮሪደሮችና የህንጻው ዙሪያ በተቋሙ በተመደበ አካል መጽዳት አለበት፡

ሸ. በተማሪዎች መኖሪያ ህንጻ ውስጥ ያሉ ዲ ኤስ ቲቪ ወይም የቴሌቪዥን ክፍሎች በቂ አየር የሚዛወርባቸው፣ መደበኛ ጽዳት የሚደረግላቸው፣ አካላዊ ርቀትን ለመጠበቅ የሚመች የወንበር አቀማመጥ ያላቸው እና ክትትልና ቁጥጥር የሚደረግባቸው መሆን አለባቸው፡፡

ቀ. ማንኛውም ተማሪ ከአንድ ብሎክ ወደ ሌላ ብሎክ መሄድ የተከለከለ ነው፡፡

10.4. የእጅ መታጠቢያ፣ የምግብ ትራፍ እና የቆሻሻ አወጋገድ

ሀ. በሁሉ ግቢዎች ውስጥ ግቢ መግቢያ በር፣ በመማሪያ ክፍሎች፣ በተማሪዎች ማደሪያ ሕንጻ መግቢያ በር፣ ቤተ-መጽሐፍት መግቢያ፣ ክሊኒክ መግቢያ፣ ቤተ-ሙከራና ወርክሾፕ መግቢያ፣ ግቢ ውስጥ ባሉ ምግብ ቤቶች መግቢያ፣ የተማሪዎች መዝናኛ ቦታዎች፣ በአስተዳደር፣ የኮሌጅ፣ ፋኩልቲ፣ ትምህርት ቤት፣ ኢንስቲትዩት እና የትምህርት ክፍሎች ህንጻ መግቢያ፣ የምርምር ማዕከላት መግቢያ እና ሌሎች የግቢ ማህበረሰብ እንቅስቃሴ በሚበዛባቸው ቦታዎች አካባቢዎች ላይ ከእጅ ንኪኪ ነጻ የሆኑ የእጅ መታጠቢያዎች አገልግሎት እንዲሰጡ መደረግ አለበት፡፡

ለ. የእጅ መታጠቢያዎቹ አካባቢዎች ተጫማሪ ቆሻሻ እንዳያስከትሉ በቂ የፍሳሽ ቆሻሻ ማስወገጃ ጋር የተቀናጁ መሆን አለበት፡፡

ሐ. የደረቅ ቆሻሻ በየወቅቱ በተደራጀ አግባብ ተሰብስቦ መወገድ አለበት፡፡ ለዚህም በሁሉም መማሪያ ክፍሎች፣ ዶርሞች፣ ቤተ-መጽሐፍት፣ ቤተ-ሙከራዎች፣ ግቢ ወስጥ የሰው እንቅስቃሴ በሚበዛባቸው ቦታዎች ሁሉ ላይ የደረቅ ቆሻሻ ማስወገጃ ቅርጫቶችን ማስቀመጥ፣ በአግባቡ ማስወገድና መልሶ ቆሻሻ ከመሰብሰብ በፊት በጸረ-ተዋህሳ ኬሚካል እንዲጸዱ መደረግ አለበት፡፡

መ. ከተማሪዎች ክሊኒክ፣ እና ሌሎች ዶርም የሚወጡ ደረቅና ፍሳሽ ቆሻሻ ኮቪድ-19 ለመከላከል የሚደረገውን ጥንቃቄ ታሳቢ አድርገው መወገድ አለባቸው፡፡

ሠ. የተማሪዎች ምግብ ቤት እና ሌሎች ግቢ ውስጥ ካሉ ምግብ ቤቶች የሚወጡ ትራፊ ምግቦች ለሌላ ለማንኛውም አካል ሳይተላለፉ በጥንቃቄ መወገድ አለባቸው፡፡

10.5. የልብስ ማጠቢያ ቦታዎች ዝግጅትና ቆሻሻ አወጋገድ

ሀ. በሁሉም ከምፓስ በቂ የልብስ ማጠቢያ ቦታዎች የተማሪዎችን አካላዊ ርቀትን ለመጠበቅ በሚመች መልኩ መዘጋጀት አለበት፡፡

ለ. የልብስ ማጠቢያ አካባቢዎች ንጽህናቸው የተጠበቀና የፍሳሽ ቆሻሻ አወጋገዱ በጥንቃቄ አከባቢን በማይበክልና ተጨማሪ የንኪኪ ዕድል በማይፈጥር መልኩ የተዘጋጀ መሆን አለበት፡፡

ሐ. በቂ የልብስ ማስጫዎችን ማዘጋጀትና አላስፈላጊ ንኪኪ እንዳይኖር ተከታታይ ቁጥጥር የሚያደርግ አካል መመደብ አለበት፡፡

መ. ማንኛውም ተማሪ ልብስ ለማስጣት ከተፈቀደለት ልብስ ማስጫ ውጪ (ለምሳሌ ሳር ላይ፣ አጥር ላይ፣ የዶርም መስኮት እና የመሳሰሉት ቦታዎች ላይ) ማስጣት የተከለከለ ነው፡፡

ሠ. ማንኛውም ተማሪ የተጠቀመበትን የጋራ የልብስና ጫማ ማጠቢያ ቦታ በአግባቡ ሳሙና በመጠቀም ማጽዳት አለበት፡፡

ረ. ማንኛውም ተማሪ ልብስና ጫማ ለማጠብ የተጠቀመበትን ቁሳቁስ በአግባቡ ማስወገድ አለበት፡

ክፍል አምስት

የኮቪድ-19 ተጠርጠሪና ታማሚ አያያዝ እና ሞት ቢከሰት ሊወሰዱ የሚገባቸው ጥንቃቄዎች

አንቀጽ 11፡- የኮቪድ-19 ተጠርጠሪና ታማሚ አያያዝ

11.1. ማንኛውም ተቋም የኮቪድ-19 ተጠርጣሪ የሚከታተል ግብረ ኃይልና የአሠራር ስርአት ሊኖረው ይገባል፡፡

11.2. የኮቪድ-19 ተጠርጣሪና ታማሚ ሲገኝ የጤና ሚኒስቴር ባወጣው መመሪያ መሠረት የሚፈጸም ይሆናል፡፡

11.3. የግብረ ኃይሉ ተጨማሪ ዝርዝር ተግባርና ኃላፊነት በተቋሙ ይወሰናል፡፡

አንቀጽ 12፡- ማቆያ፣ ለይቶ ማቆያ እና ህክምናን (Quarantine, Isolation and Treatment) በሚመለከት

12.1. ሁሉም ከፍተኛ ትምህርት ተቋማት በኮቪድ-19 ራሳቸውን ለሚጠረጥሩ፣ ለሚጠረጠሩ፣ እና የበሽታውን የተለያዩ ምልክቶችን ለሚያሳዩ ተማሪዎች የሚሆን የለይቶ ማቆያ ማዕከል በግቢ ውስጥ ማዘጋጀት አለበት፡፡ የሚጠረጠሩ ሲገኙም ከሚመለከታቸው የጤና ተቋማትና ባለሙያዎች ጋር በመቀናጀት የጤና ሚኒስቴር ባወጠው መመሪያ መሠረት አስፈላጊውን ክትትልና ድጋፍ ማድረግ አለበት፡፡

12.2. ማንኛውም የከፍተኛ ትምህር ማህበረሰብ አባል ኮቪድ-19 ያለበት መሆኑ በምርመራ ውጤት ሲረጋገጥ ከሚመለከታቸው የጤና ተቋማት ጋር በመቀናጀት ከግቢ ውጭ ባሉ የህክምና ማዕከላት እንዲረዳ መደረግ አለበት፡፡

አንቀጽ 13፡- በኮቪድ-19 ምክንያት ሞት ብከሰት

በከፍተኛ ትምህርት ተቋም በኮቪድ-19 ምክንያት ሞት ብከሰት የሬሳ አያያዝ፣ ማጓጓዝና የቀብር ስነ-ስርዓት በጤና ሚኒስቴር በወጣው መመሪያ መሠረት የሚፈጸም ይሆናል፡፡ ሂደቱም በጤና ባለሙዎች ግብረ ኃይል ተሳትፎ የሚመራ ይሆናል፡፡

ክፍል ስድስት

የባለድርሻ አካላት ሚና

ይህ ክፍል የከፍተኛ ትምህርትና ስልጠና ተቋማት በኮቪድ ወረርሽኝ ወቅት የባለድርሻ አካላትን ሚና የሚዘረዝር ነው፡፡ መመሪያውን በተገቢዉ መንገድ ለመፈጸም የተለያዩ ባለ-ድርሻ አካላትን ንቁ ተሳትፎና ቅንጅታዊ አሰራር ይፈልጋል፡፡ የሳይንስና ከፍተኛ ትምህርት ሚኒስቴር ስራዉን በበላይነት በማስተባበርና በመምራት ቁልፍ ሚና የሚጫወት ይሆናል፡፡ በተቋም ደረጃ የተቋማት ቦርድ አመራሮች፣ የተቋማቱ የበላይ አመራሮች እንዲሁም የሚመለከታቸዉ የክልልና የዞን/ወረዳ መሰተዳድር አካላት ትምህርቱና ስልጠናውን የማስቀጠል ስራ ሰላማዊ እና ዉጤታማ ለማድረግ የበኩላቸዉን ሚና የሚወጡ ይሆናል፡፡

አንቀጽ 14፡- በባለድርሻ አካላት የሚከናወኑ ዋና ዋና ተግባራት

14.1. በሳይንስና ከፍተኛ ትምህርት ሚኒስቴር የሚከናወኑ ተግባራት

14.1.1. የተጓደሉ የቦርድና የተቋማት የበላይ አመራሮች እንዲሟሉ ያደርጋል፤

14.1.2. በኮረና (COVID-19) ጊዜና ድህረ-ኮረና (COVID-19) ትምህርትና ስልጠናን ለማስቀጠል የሚያስችል ስልቶችን በመንደፍ በሚመለከተዉ የሚኒስቴር መስሪያቤቱ ማኔጅመንት ይሁንታ እንዲያገኝ በማድረግ ተግባራዊ ያደርጋል፡፡

14.1.3. ለአመራር ቦርድ አባላት፣ ለክልል የቴ/ሙ/ት/ስ/አመመራሮች፣ለከፍተኛ ትምህርትና ስልጠና ተቋማት አመራሮችና ተቋማቱ ላሉበት አከባቢ አስተዳደር አመራሮች ግንዛቤ በመፍጠር ስምሪት ይሰጣል/ያስተባብራል፤

14.1.4. የድጋፍና ክትትል ግብረ- ሃይል በማደራጀት በየተቋማቱ የተቋረጠዉን ትምህርትና ስልጠና ለማስጀመር አስቻይ ሁኔታዎች መኖራቸውን ያረጋግጣል፤ከሚመለከታቸው የክልል ቴ/ሙ/ት/ስ/ አመራሮች ጋር በጋራ ይሰራል

14.1.5. ወረርሽኙን እየተቆጣጠሩ የመማር ማስተማሩን ስራ ያለስጋት መተግበር ይቻል ዘንድ ኢጋሮችና ባለድርሻ አካላት ከንጽህና መጠበቂያ ቁሶች ጀምሮ ሌሎች የመማር ማስተማሩን በቴክኖሎጂ ለማስደገፍ የሚያስችሉ ሌሎች ልዩ ልዩ ድጋፎችን ለየተቋማቱ እንዲያደርጉ ያበረታታል፤

14.1.6. በኮሮና ወረርሽኝ ምክንያት የተቋረጠዉን የ2012 ዓ.ም ትምህርትና ስልጠና በተያዘው የክራሽ ፕሮግራም ጊዜ ውስጥ ለማጠናቀቅ ለሚደረገው ርብርብ ተቋማቱ ልዩ ድጋፍ ስለሚያገኙበት መንገድ ከሚመለከታቸው የመንግስት አካላት ጋር ምክክር ያደርጋል፤

14.1.7. ለሰላማዊ መማር ማስተማርና በኮሮና ወቅት የማስፈጸሚያ መመሪያ ያወጣል

14.1.8. የመማር ማስተማር ሂደቱን ሰላማዊ በሆነ መንገድ ለማስኬድ የሚያስችል ሁኔታ ስለመኖሩ ግምገማና ክትትል ያደርጋል፡፡

14.2. የከፍተኛ ትምህርትና ስልጠና ተቋማት ሥራ አመራር ቦርድ ሚና

የከፍተኛ ትምህርትና ስልጠና ተቋማትን በበላይነት የመምራት ኃላፊነት የተጣለበት የየተቋማቱ ስራ አመራር ቦርድ ከተለመደው አመራር ለየት ባለ ተነሳሽነትና ትኩረት የሚከተሉትን ተግባራት እንዲያከናውን ይጠበቃል፡፡

14.2.1. የሁሉም ተቋማት ቦርድ የራሱ የሆነ በኮረና (COVID-19) ጊዜና ድህረ-ኮረና (COVID-19) የከፍተኛ ትምህርትና ስልጠና የመማር ማስተማር ስራ የሚመራበትን ልዩ ዕቅድ ያዘጋጃል አተገባበሩንም ይከታተላል፤

14.2.2. የአመራር ከፍተት ያለበትን ቦታ በመለየት በተሻለ ፍጥነት ከሚኒስትሩ ወይም ከክልል የቴ/ሙ/ት/ስ/ አመራሮች ጋር በመመካከር በልዩ ሁኔታ የማሟላት ስራ ይሰራል፤

14.2.3. በኮረና (COVID-19) ጊዜና ድህረ-ኮረና (COVID-19) የመማር ማስተማሩን ስራ ለማስቀጠል ከተለያዩ ምንጮች ሀብት የማሰባሰቢያ ስልቶችን በመቀየስ ድጋፍ ማድረግ፣

14.2.4. ተቋማቱ በኮረና (COVID-19) ጊዜና ድህረ-ኮረና (COVID-19) መማር ማስተማሩን ማስቀጠል የሚያስችል ዕቅድ እንዲያዘጋጁ ያደርጋል ለአፈጻጸሙም ድጋፍና ክትትል ያደርጋል፤

14.2.5. ትምህርትና ስልጠናዉን በማስቀጠል ሂደት የሚያጋጥሙ የተለያዩ ችግሮችን ከባለ ድርሻ አካላት ጋር በመተባበር ፈጣን ምላሽ ይሰጣል፡፡

14.2.6. የመማር ማስተማር ሂደቱ ሰላማዊ በሆነ መንገድ ለማስከሄድ የሚያስችል ሁኔታ ስለመኖሩ ይገመግማል፤ ክትትል ያደርጋል፡፡

14.2.7. ሃላፊነታቸውን በአግባቡ መወጣት ያልቻሉ አመራሮች ላይ እርምጃ ይወስዳል

14.3. የተቋማት የበላይ ኃላፊዎች ሚና

14.3.1. የመማር ማስተማር ስራዎችን የሚከታተል ግብረ-ሃይል በማደራጀት ወደ ስራ ያስገባሉ፤

14.3.2. በ2012 ዓ.ም የትምህርት ዘመን በኮሮና ወረርሽኝ ምክንያት ትምህርት ከመቋረጡ በፊት የኮርሶች/ሞጁሎች አፈጻጸም የነበረበትን ደረጃ በፕሮግራም፣ በድፓርትመንት፣ በፋኩልቲ እና በተቋም ደረጃ በጥልቀት በመገምገም ከኮርሶቹ/ሞጁሎቹ ባህርይ እንዲሁም ከጊዜ ገደብና ከሀብት (ወጪ) አንጻር የተቀናጀ ዝርዝር እቅድ ማዉጣትና የአፈጻጸም መርሃ-ግብር በሚለከተዉ አካል በማዘጋጀት በሴኔት ማስጸደቅና ወደ ስራ ያስገባሉ፣

14.3.3. በ2012 ዓ.ም የትምህርት ዘመን በኮሮና ወረርሽኝ ምክንያት የተቋረጠዉን ትምህርት ለማስቀጠል የተዘጋጀዉን ዕቅድና የአፈጻጸም መርሀ-ግብር በተቋሙ ያሉ ሰራተኞች የጋራ ግንዛቤ እንዲይዙ ያደርጋሉ፤

14.3.4. በ2012 ዓ.ም የትምህርት ዘመን የተቋረጠዉን ትምህርት በክራሽ ፕሮግራም ለማጠናቀቅ የተከለሰ ካላንደር በማዘጋጀትና በሴኔት በማጸደቅ ለሚመለከታቸዉ ሁሉ ተደራሽ በማድረግ በየደረጃው በቂ ዝግጅት መደረጉን ይከታተላሉ፤

14.3.5. በ2012 ዓ.ም የትምህርት ዘመን የተቋረጠዉ ትምህርትና ስልጠና በተቀመጠዉ መርሃ-ግብር መሰረት ለማጠናቀቅ የሚያስችል የሰዉ ሃይል (መምህራን/አሰልጣኞች፣ የላቦራቶሪ ቴክኒሽያን...) እና ሌሎች ግብዓቶች መሟላታቸውን ያረጋግጣሉ፣

14.3.6. ሁሉም የትምህርትና ስልጠና ተቋማት በክራሽ ለሚሰጡ ኮርሶች/ሞጁሎች የትምህርት ጥራቱን በምንም መልኩ በማይጎዳ ሁኔታ የኮርሱ ዋና ዋና የብቃት አሃዶች (Core competencies) ማስጨበጥ

በሚያስችል ሁኔታ የማስተማሪያ/ዶኩሜንት ወይም ኢጋዥ ሌክቸሮችን ወይም ሃንዳውቶችን/TTLM፣ ከገላጭ ፓዎር ፖይንት ጋር በሶፍት ኮፒና በሀርድ ኮፒ እንዲያዘጋጁ ያደርጋሉ፤

14.3.7. መምህራን/አሰልጣኞች የኮረስ አዉትላይን፣ ማስተማሪያ፣ መልመጃዎች፣ ማጣቀሻና ኢጋዥ መጽፍትን በሶፍት ኮፒና በሀርድ ኮፒ (በድምጽ እና በምስል) እንዲያሰባስቡና ከሚስተምሩት ትምህርት ጋር አደራጅተውና አቀናጅተው ለተማሪዎች ተደራሽ ማድረጋቸውን ያረጋግጣሉ፤

14.3.8. ተማሪዎች/ሰልጣኞች ከተለመደዉ መደበኛዉ ፕሮግራም በአጠረ የክራሽ ፕሮግራም ትምህርትና ስልጠናቸዉን ለማጠናቀቅ በመገደዳቸው ልዩ የጋይዳንስና ካውንስሊንግ አገልግሎት እንዲሁም አካዳሚያዊ የምክር አገልግሎት እንዲያገኙ የሚያስችል የአሰራር ስርዓትን ተግባራዊ ያደርጋሉ፤

14.3.9. ከትምህርት ክፍል እስከ የተቋሙ የበላይ አመራሮች ያለውን የግንኙነት ስርዓትን በማጠናከር የክትትልና ድጋፍ ስርዓቱ ፈጣንና ችግሮች ሲፈጠሩም ተገቢውን የእርምት እርምጃ ለመውሰድ የሚያስችል ስርዓት ይዘረጋሉ፤

14.3.10. ተማሪዎች/ሰልጣኞች መማር ማስተማሩን አስመልክቶ ለሚኖራቸው ቅሬታ በአስቸኳይ መፍትሄ ሊሰጥ የሚችል ግብረ-ኃይል ያደራጃሉ፤

14.3.11. የተማሪዎች/ሰልጣኞች ወደ ተቋማት ሲመለሱ በተሻለ ፍጥነት ጥሪ ያደርጋሉ እንድሁም የምረቃ፣ ሠርቲፊኬት እና ሌሎች ተያያዥ ስራዎችን የማስፈጸሚያ እቅድ አዘጋጅቶ ተግባራዊ ያደርጋሉ፤

14.3.12. የተግባር ትምህርት እና ምዘና ያላቸዉ ተመራቂ ተማሪዎች/ሰልጣኞች ባሉበት ተቋማት ከሚመለከታቸዉ ባለድርሻ አካላት ጋር በመመካከር በክራሽ ፕሮግራሙ ወቅት እንዴት መምራት እንደሚገባቸዉ በዓይነቱ ልዩ የሆነ ዝርዝር የአፈጻጸም ዕቅድ በማዘጋጀት ይተገብራሉ፤

14.3.13. የአስተዳደር ስራዎችን የሚከታተል ግብረ-ሃይል በማደራጀት ካለዉ መዋቅር ጋር በማቀናጀት ወደ ስራ በማስገባት ከኮሮና እና ሰላማዊ መማር ማስተማር ጋር የተያዙ ጉዳዮችን ለመከታተል ዝርዝር ዕቅድ ያዘጋጃሉ፤

14.3.14. ቫይረሱን ለመከላከል የተቀመጡ የጥንቃቄ መንገዶችን በባነር፣ በፖስተር፣ በስክሪን ወዘተ በማዘጋጀት በሚታዩ ቦታዎች ላይ ተደራሽ እንዲሆኑ ያደርጋሉ፣

14.3.15. ቫይረሱን ለመከላከል የተቀመጡ የጥንቃቄ መንገዶችን አለመከተል ተጠያቂነትን የሚያስከትል መሆኑን በግልጽ በማሳወቅ ከቅበላ በፊት በሚኒስቴር መስሪያ ቤቱ በኩል በህዝብ መገናኛ ብዙሃን እና በተቋማት ለተማሪዎችና ለተቋሙ ማህበረሰብ ግልጽ መደረጉን ያረጋግጣሉ፣

14.3.16. ተማሪዎች/ሰልጣኞች ግቢ ዉስጥ እስካሉና ወረርሽኙ እስካልጠፋ ድረስ ዉሃ፣ ሳንታይዘር፣ ማስክ እና ሳሙና ያለ እጅ ንክኪ ጥቅም ላይ መዋላቸውን ያረጋግጣሉ፣

14.3.17. በ2012 ዓ.ም የትምህርት ዘመን በኮሮና ወረርሽኝ ምክንያት የተቋረጠዉን ትምህርት ለማጠናቀቅ የሚያስችል በጀት በልዩ ሁኔታ ማግኘት የሚቻልበትን ስልት ይቀይሳሉ፤

14.3.18. የግዥና ንብረት አስተዳደር ሥራዎችን በተመለከተ መገዛት የሚገባቸዉ ቁሶች (የተማሪዎች ምግብ፣ የላቦራቶሪ ኬምካሎች፣ የላቦራቶሪ ዕቃዎች፣ የዎርክሾፕ ማቴሪያሎች፣ የማስተማሪያ ቁሳቁሶች፣ ሳንታይዘሮች፣ የፊት መሸፈኛ ጭምብሎች፣ የእጅ ጓንቶች፣ ከንክኪ ነጻ የእጅ መታጠቢያ ማሽኖች ወዘተ) በአግባቡ በመለየት በጊዜዉ ጨረታ በማዉጣትና ዉሎችን በመፈጸም ፈጣን ግዥዎችን ማከናወን የሚያስችል አሰራር ይዘረጋሉ፤

14.3.19. ስራዎችን ለማሳለጥ የሚያስችሉ አሠራር ስርዓቶች፣ የተከኖሎጂ እና ሌሎች መሠረተ ልማት ምቹ ሁኔታ ተቋማዊ በሆነ መልኩ መፈጠሩን ያረጋግጣሉ፤

14.3.20. ዝርዝር ስራዎችን በየጊዜዉ ይገመግማሉ ፈጣን የማስተካከያ እርምጃዎችን ይወስዳሉ፤

14.3.21. ለማቆያነት ሲያገለግሉ የነበሩ ተቋማት በኬሚካል ማጽዳትና ለአገልግሎት ዝግጁ እንዲሆኑ ያደርጋሉ፤

14.3.22. ተማሪዎች/ሰልጣኞች ወደ የተቋማቱ ሲጠሩ በጉዞ ሂደት ለወረርሽኙ ተጋላጭ እንዳይሆኑ የሚታደግ የትራንስፖርት አገልግሎት ያገኙ ዘንድ ከትራንስፖርት ሚኒስቴርና በየደረጃው ካሉ ቅርንጫፍ ጽ/ቤቶች ጋር በቅንጅት ይሰራሉ፤

14.3.23. የቫይረሱ ምልክት በተቋም ደረጃ ቢታይ (ተጠርጣሪ ቢገኝ) በግቢ ዉስጥ የለይቶ ማቆያና ልዩ ህክምና መስጫ ማዕከል መኖሩን ያረጋግጣሉ፣ እንድሁም በየተቋማቱ ከሚገኙ የተማሪዎች ክሊኒክ፣ ከዞን/ወረዳ ጤና ማዕከላት ጋር በቅርበት ይሰራሉ፣

14.3.24. የመመገቢያ ሰዓትን በማራዘም፣ ተማሪዎች/ሰልጣኞች በመመገቢያ አዳራሽ ርቀታቸዉን ጠብቀዉ የሚመገቡበት ሁኔታ ያመቻቻሉ፣

14.3.25. ቫይረሱ በተቋም/በካምፓስ ደረጃ በወረርሽኝ መልክ ቢስፋፋ ከሚመለከታቸዉ ባለድርሻ አካላት ጋር በመመካከር አስፈላጊዉ እርምጃ እንዲወሰድ ያደርጋሉ፣

14.3.26. የመማር ማስተማር ሂደቱ ሰላማዊ በሆነ መንገድ ለማስከሄድ የሚያስችል ሁኔታ ስለመኖሩ ግምገማና ክትትል ያደርጋሉ፣

14.3.27. ተማሪዎች በየጊዜዉ አስፈላጊዉን የጤና ምርመራና ክትትል እንዲደረግላቸዉ ያደርጋሉ፣

14.3.28. ለተማሪዎች የተለያዩ አገልግሎት የሚሰጡ መምህራንና ሰራተኞች አስፈላጊዉ የጤና ምርመራና ክትትል እንዲደረግላቸዉ ያደርጋሉ፣

14.3.29. ሃላፊነታቸውን በአግባቡ ባልተወጡ የቢታች አመራሮች፣ መምህራን/አሰልጣኞች፣ ተማሪዎች/ሰልጣኞችና አስተዳደር ሰራተኞች ላይ አስፈላጊውን እርምጃ ይወስዳሉ

14.4. የመምህራን/አሰልጣኞች ሚና

14.4.1. የተቋረጠውን ትምህርትና ስልጠና ለማስቀጠል የሚያስፈልጉ ዝግጅቶችን ለምሳሌ የሞጁል ዝግጅት፣ የዎርክሾፖችን የማደራጀት፤ በቴክኖሎጂ የታገዘ ትምህርትና ስልጠና ለመስጠት የሚያስችል ዝግጅቶችን ያደርጋሉ

14.4.2. በሚደረግላቸው ጥሪ መሰረት በስራ ቦታቸው በመገኘት ኮቪድን ለመከላከል የሚያስችሉ ድንጋጌዎችን እና የተቀመጡትን ክልከላዎች በመተግበር ትምህርትና ስልጠናውን ያከናውናሉ

14.4.3. በጤና ሚኒስተርና በሳ.ኪ.ት.ሚ. የሚወጡ ጠኮሮና ቫይረስ ስርጭትን ለመቆጣጠርና ለመከላከል የተዘጋጁ መመሪያዎችን ተማሪዎች/ሰልጣኞች እንዲተገብሩ ያደርጋሉ

14.4.4. በተሰጠው ጊዜ ውስጥ ተማሪዎች/ሰልጣኞች ትምህርታቸውን/ስልጠናውን እንዲያጠናቅቁ ከተለመደው ተጨማሪ ጊዜን ስራ ላይ በማዋል የአዲሱን ኖርማል አሰራር ተግባራዊ ያደርጋሉ

14.4.5. የተማሪዎችን/ሰልጣኞችን ውጤት በጊዜ ለሚመለከተው የስራ ክፍል ሪፖርት ያደርጋሉ፤ በውጪ አካል የሚመዘኑ ሰልጣኞችንም በመለየት ዝርዝራቸውን ለሚመለከተው አካል ያቀርባሉ፤

14.4.6. በምዘና ብቁያልሆኑ ወይም ልዩ ድጋፍ የሚፈልጉ ተማሪዎችን/ሰልጣኞችን ድጋፍ በማድረግ እንዲበቁ ያደርጋሉ፡፡

ክፍል ሰባት

ይህን መመሪያ በሚጥሱ ተቋማትና የተቋማቱ ማህረሰብ ላይ የሚወሰዱ እርምጃዎች

አንቀጽ 15፡- እርምጃ የሚወሰድባቸው አካላት

15.1. ተቋም

15.2. የተቋም አመራር

15.3. መምህራን

15.4. አስተዳደር ሠራተኞች

15.5. ተማሪዎች

15.6. ሌሎች በግቢ ውስጥ አገልግሎት የሚሰጡ ግለሰቦች፣ ተቋማት ወይም ማህበራበት ይሆናሉ፡፡

አንቀጽ 16፡- የጥፋት ምድብና የሚያስከትለው የቅጣት ዓይነት

16.1. የጥፋት ዓይነቶች በጥፋቶቹ ደረጃና ድግሞሽ ልክ አነስተኛ፣ ቀላል፣ መካከለኛ፣ ከፍተኛ ወይም በጣም ከፍተኛ ተብለው የሚመደቡ ይሆናል፡፡

16.2. ጥፋት ቅጣት ዓይነቶች

በዚህ መመሪያ መሠረት ጥፋት በፈጸመ የከፍተኛ ትምህርና ስልጠና ማህበረሰብ አባል ላይ ሊወሰድ የሚችል ቅጣትና እርምጃ፡

16.2.1. የቃል ግሳጼ፤ በጽሑፍ የሚሰጥ የቃል ማስጠንቀቂያ

16.2.2. የጽሑፍ ማስጠንቀቂያ (ቀላል፣ ከባድና የመጨረሻ)

16.2.3. ስለ ጉዳዩ ለቤተሰብ ማሳወቅ

16.2.4. ማህበራዊ አገልግሎት የሚያሰጥ ቅጣት፣
16.2.5. ጥፋት የፈፀመበትን ንብረት መውረስና በጥፋቱ የተጎዱ ወይም ዋጋቸው የቀነሰ፣ ወይም ሙሉ በሙሉ የወደሙ ንብረቶች ወይም ሕንፃዎች፣ ተገጣጣሚዎች ካሉ የሚተኩ ከሆኑ እንዲተኩ ማድረግ፣ ካልሆነ ዩኒቨርሲቲው በባለሙያ አስጠንቶ በሚያቀርበው የወቅቱ የገበያ ዋጋ መሠረት ዋጋውን ማስከፈል
16.2.6. የወር ደመወዝ ቅጣት
16.2.7. ከኃላፊነት ቦታ ማስነሳት
16.2.8. ከኃላፊነት ቦታዎች ውድድር መታገድ ወይም በድጋሚ በኃላፊነት ቦታዎች እንዳይሰም ማገድ
16.2.9. ደረጃ ዝቅ ማድረግ
16.2.10. ለተወሰነ ጊዜ ከትምህርት ዕድልና የደረጃ ዕድገት፣ የደመወዝ ለውጥ ወይም ጥቅማ ጥቅም ማገድ
16.2.11. ለተወሰነ ጊዜ ከትምህርት ማገድ
16.2.12. የትምህርት ማስረጃውን ለተወሰነ ጊዜ መያዝ
16.2.13. የትምህርት ማስረጃ ፈጽሞ አለመስጠት
16.2.14. ሙሉ በሙሉ መሰናበት
16.2.15. ጉዳዩን በወንጀል ወይም በፍታብሔር ሕግ እንዲታይ ለሚመለከተው አካል ማስተላለፍ

የጥፋት ምድብ	እርምጃ የሚወሰድባቸው አካላትና የቅጣት ዓይነት			
	ተማሪዎች	መምህራን	አስተዳደር ሰራተኛ	አመራር
አነስተኛ	• ምክር • የቃል ማስጠንቀቂያ	የጽሑፍ ማስጠንቀቂያ	• ምክር • የጽሑፍ ማስጠንቀቂያ	ከባድ የጽሁፍ ማስጠንቀቂያ
ቀላል	• ጽሑፍ ማስጠንቀቂያ እስከ • ከባድ የጽሁፍ ማስጠንቀቂያና 30-50 ሰዓት ማህበራዊ አገልግሎት	• ከባድ የጽሁፍ ማስጠንቀቂያ • የአንድ ወር ደመወዝ ቅጣት	• ከባድ የጽሁፍ ማስጠንቀቂያ • የአንድ ወር ደመወዝ ቅጣት	• የመጨረሻ የጽሑፍ ማስጠንቀቂያ • የአንድ ወር ደመወዝ ቅጣት
መካከለኛ	ከአንድ ወሰነ ትምህርት እስከ ሁለት ዓመት የሚያስቀጡ	• የመጨረሻ የጽሑፍ ማስጠንቀቂያና • የሶስት ወር ደመወዝ ቅጣት	• የመጨረሻ የጽሑፍ ማስጠንቀቂያና • የሶስት ወር ደመወዝ ቅጣት	• ከኃላፊነት ቦታ ማስነሳት • የሶስት ወር ደመወዝ ቅጣት • እስከ 5ዓመት ከኃላፊነት ቦታዎች ውድድር መታገድ
ከፍተኛ	ከሁለት ዓመት እስከ ሶስት ዓመት የሚያስቀጡ (ከትምህርት ገበታ የሚያሳግዱ) ጥፋቶች	• አንድ ደረጃ ዝቅ ማድረግ እና 3 ወር ደመወዝ ቅጣት • ከ2-3 ዓመት ○ ከትምህርት ዕድልና የደረጃ ዕድገት፣ ○ የኃላፊነት ቦታ ውድድር፣ ○ የደመወዝ ለውጥ ○ ጥቅማ ጥቅም መታገድ	• አንድ ደረጃ ዝቅ ማድረግ • ከ2-3 ዓመት ○ ከትምህርት ዕድልና የደረጃ ዕድገት ውድድር፣ ○ የኃላፊነት ቦታ ውድድር፣ ○ የደመወዝ ለውጥ ○ ጥቅማ ጥቅም መታገድ	• ከኃላፊነት ቦታ ማስነሳት • አግባብነት ባለው ሕግ መጠየቅ • በድጋሚ በኃላፊነት ቦታዎች አይሰየምም • ከ2-3 ዓመት፡- ○ የደረጃ ዕድገት ውድድር፣ ○ የደመወዝ ለውጥ ○ ጥቅማ ጥቅም መታገድ
በጣም ከፍተኛ	• ከዩኒቨርሲቲው የትምህርት መርሃ-ግብር ሙሉ በሙሉ መሰናበት • ለ2ዓመት በየትኛውም የትምህርት ተቋም መማር አይችልም	• ከሥራ ገበታ ሙሉ በሙሉ መሰናበትን የሚያስከትሉ • መምህር እስከ 3ዓመት በየትኛውም የትምህርትና ስልጠና ተቋማት ውስጥ በቋሚነትም ሆነ በግዜያዊነት ቅጥር መፈጸም አይችልም::	ከሥራ ገበታ ሙሉ በሙሉ መሰናበት	• ከሥራ ገበታ ሙሉ በሙሉ መሰናበት • አግባብነት ባለው ሕግ መጠየቅ

አንቀጽ 17፡- አነስተኛ ጥፋቶች

17.1. በምክር የሚታለፉ ጥፋቶች፣

17.1.1. የመመገቢያ እቃዎችን በተገቢው ቦታ ያለማስቀመጥ /ያለመመለስ/

17.1.2. በልዩ ሁኔታ የሚፈቀድላቸው ካልሆኑ በስተቀር አገልግሎት መስጫ ቦታዎች ላይ ርቀትን ጠብቆ አለመሰለፍ ወይም ተራን አለመጠበቅ፤

17.1.3. ለመጀመሪያ ጊዜ አልኮል ጠጥቶ ሰክሮ ወደ ግቢ መግባት፣

17.1.4. ባልተፈቀደ ቦታ ማናቸውንም ማስታወቂያ መለጠፍ

17.1.5. በመኝታ ክፍል ውስጥ ተገቢ ያልሆነ ጽሑፍ እና/ወይም ስዕል መለጠፍ፣

17.1.6. የመማሪያ ክፍሎች፣ የአዳራሾችና የአገልግሎት መስጫ ክፍሎች ወንበሮችና ጠረንጴዛዎች ለመጀመሪያ ጊዜ ከቦታ ቦታ ማዛወር፣ አውጥቶ ደጅ ጥሎ መሄድ፣

17.1.7. ሌሎች መሰል የሥነ-ምግባር ጥፋቶችን መፈጸም፣

17.2. የቃል ማስጠንቀቂያ የሚያሰጡ ጥፋቶች

የቃል ማስጠንቀቂያ የሚያሰጡ ጥፋቶች ሆነው በማስታወሻ መዝገብ የሚያዙ እና ግለሰቡም ለጥፋቱ የሚፈርምበት ሆኖ በጽሁፍ የሚሰጡ ናቸው፡፡

17.2.1. ከላይ የተዘረዘሩትን በምክር የሚታለፉና መሰል ጥፋቶችን በድጋሜ ለሁለተኛ ጊዜ ፈጽሞ መገኘት

17.2.2. እጅን ባልተፈቀደ ቦታ መታጠብ፣

17.2.3. በመኝታ ክፍል ውስጥና በኮሪደር፣ በእጅና ፊት መታጠቢያ ቦታዎች በመተላለፊያ መንገድ ላይ ልብስ ማጠብ፣

17.2.4. በመማሪያ ክፍሎች፣ በአብያተ መጽሀፍት፣ በመኝታ ህንፃዎችና በሌሎች የአገልግሎት መስጫ ክፍሎች ግድግዳዎች እንዲሁም በወንበሮችና ጠረጴዛዎች ላይ ማንኛውንም ጽሑፍ መፃፍ/ስዕል መሣል፣

17.2.5. ውሃና የኤሌክትሪክ ሃይል ያለአግባብ መጠቀም (ማባከን)፣ ውሃ ከፍቶና መብራት አብርቶ መሄድ፣

17.2.6. አብረው ከሚኖሩ የመኝታ ቤት ተጋሪዎችና አብረው ከሚማሩ የትምህርት ክፍል ተማሪዎች ጋር ተግባብቶና ተስማምቶ አለመኖር፣

17.2.7. ተቋሙ ባወጣው አሰራር መሰረት መታወቂያ ወይም የምግብ ካርድ እንዲያሳይ ተጠይቆ ፈቃደኛ አለመሆን፤

17.2.8. አትክልቶችንና አበባዎችን መርገጥ ወይም መቁረጥ፤

17.2.9. ፍራሽ ከአልጋ አውርዶ መገኘት፣

17.2.10. የታጠበ ልብስን ከልብስ ማስጫ ቦታ ውጭ ማስጣት፤

17.2.11. በግቢ ውስጥ ከፍተኛ ድምጽ ወይም ጩኸት በራስ ድምጽ ወይም በማንኛቸውም የኤልክትሮኒክስ መሣሪያዎች በማስጮህ የአካባቢን ፀጥታን ማደፍረስ፤ (በጫማም ይሁን በሌላ መንገድ)

17.2.12. ሌሎች መሰል የስነ ምግባር ጥሰቶችን መፈጸም፤

አንቀጽ 18፡- ቀላል ጥፋቶች

ከጽሑፍ ማስጠንቀቂያ እስከ ከባድ የጽሁፍ ማስጠንቀቂያና እንደአስፈላጊነቱ ማህበራዊ አገልግሎት በመስጠት የሚያስቀጡ ጥፋቶችን ያካትታል፡፡

18.1. የጽሑፍ ማስጠንቀቂያ ወይም ከ30 ያላነሰ ከ50 ሰዓታት ያልበለጠ ማህበራዊ አገልግሎት (የጉልበት ሥራ) ወይም በሁለቱም ሊያስቀጡ የሚችሉ ጥፋቶችን

18.1.1. ከላይ በአነስተኛ ጥፋቶች የተዘረዘሩትን የቃል ማስጠንቀቂያ ወይም ነጻ ማህበራዊ አገልግሎት የሚያሰጡ ጥፋቶች መካከል አንዱን ጥፋት ተፈፅሞ በተወሰደው ቅጣት መሻሻል ሳይታይና ያንኑ ወይም ተመሳሳይ ጥፋት ደግሞ መፈጸም፤

18.1.2. ወደ ዩኒቨርሲቲው ቅጥር ግቢ የተደነገገን የሰዓት ገደብ አለማክበር፤

18.1.3. በተራ ምድብ ወቅት የመኝታ ክፍልን፣ መጸዳጃ ቤትን፣ የመኖሪያ ሕንፃ ኮሪዶርን፣ የመኖሪያ ሕንጻ አካባቢን አለማጽዳት፣ የራስን አልጋ አለማንጠፍና የግል ንጽህናን አለመጠበቅ፣

18.1.4. ግለሰቦችን ለተራ ጥል መጋበዝ፣ ማጣላት፣ ነገር መቆስቆስ፣ ማጋጋል፣ ጥል ሲነሳ አለመገላገል፣ ወገን ለይቶ ማበር፣ በነገር ማቆራቆስ፣

18.1.5. ከተፈቀደ ቦታ ውጭ በዩኒቨርሲቲው ግቢ ውስጥ ቆሻሻ መጣል፤

18.1.6. በዩኒቨርሲቲው ተገቢ አካል የተሰጠን ሕጋዊ ትእዛዝ አለማክበር፤
18.1.7. ለጋራ ጤንነት አደገኛ የሆኑ ድርጊቶችን መፈጸም፤
18.1.8. ያለ ግለሰቡ ወይም ዩኒቨርሲቲው ፈቃድ የግለሰብ ወይም የዩኒቨርሲቲ ንብረት መጠቀም፣
18.1.9. የሌላ ሰው መታወቂያ ወይም የምግብ ካርድ መጠቀም፣
18.1.10. የተማሪዎች አገልግሎት እና የተማሪዎች ህብረት ሳያውቁ በየትኛውም መንገድ ከተማሪዎች ገንዘብ መሰብሰብ፣
18.1.11. የተማሪዎችን ትራንስፖርትና የመሳሰሉ አገልግሎቶችን በማመቻቸት ሽፋን ለግል ጥቅም ሲባል ተማሪዎችን ከፍተኛ ክፊያ መጠየቅ ወይም እንዲጠየቁ መተባበር፣
18.1.12. በተቋሙ ግቢ ውስጥ ሲጋራ ማጨስ፤ ሌሎች አደንዛዥ ዕጾችን መጠቀም ወይም ይዞ መገኘት፤ ሌሎችም አጭሰው ወይም ይዘው እያዩ ዝም ማለት
18.1.13. የጋራ መገልገያዎችን አለአግባብ ለግል ጥቅም ማዋል፣
18.1.14. አጭበርብሮ የገንዘብ ድጋፍ ከዩኒቨርሲቲው ለማግኘት መሞከር፣
18.1.15. ምንም ውክልና ሳይኖር የተማሪዎች ህብረት አባል፣ የክበብ ተጠሪ ነኝ ወዘተ በማለት ሰዎች መረጃ እንዲሰጡት መጠየቅ ወይም መስራት፣

18.2. ከባድ የጽሁፍ ማስጠንቀቂያና እንደአስፈላጊነቱ ማህበራዊ አገልግሎት በመስጠት የሚያስቀጡ ጥፋቶች
18.2.1. ከላይ የጽሑፍ ማስጠንቀቂያ ወይም ከ30 ያላነሰ ከ50 ሰዓታት የሚያስቀጡ ጥፋቶች መካከል አንዱን ወይም ተመሳሳይ ጥፋት ፈፅሞ በተወሰደው ቅጣት መሻሻል ሳያሳዩ ያንኑ ወይም ተመሳሳይ ጥፋት ደግሞ መፈጸም፤
18.2.2. በግቢው ውስጥ በተለይም በጋራ መገልገያ አካባቢዎች ማለትም በመኝታ፣ በመመገቢያና በመማሪያ ክፍሎች፣ በቤተ መፃህፍት፣ በወርክሾፖች፣ በቤተሙከራ በክሊኒክና በዲ.ኤስ.ቲቪ ወዘተ አካባቢ ያልተገባ ጩኸት ማሰማት፣ ሁከትና ግርግር ማንሳት፣
18.2.3. በመጠጥ ሀይል ሰክሮ በግቢው ውስጥ ሁከት መፍጠር (የአካባቢ ፀጥታን ማደፍረስ)፣
18.2.4. በተቃራኒ ፆታ መኝታ ህንፃ ውስጥ ያለ ፈቃድ ገብቶ መገኘት፣
18.2.5. ፍራሽ ወይም ትራስ ወይም የፍራሽ ልብስ ቀዶ መገኘት፣
18.2.6. ባልተፈቀደለት መኝታ ቤት ማደር ወይም የመኝታ ቦታን ያለፈቃድ መቀየር
18.2.7. ያልተፈቀደለት ሰው በመኖሪያ ቦታ እንዲኖር፣ እንዲዳበል ወይም እንዲያድር ማድረግ፤
18.2.8. ያለፈቃድ የበሰለ ምግብ ከዳቦ ውጭ ከማንኛውም ቦታ ወደ ዶርም ይዞ ገብቶ ሲጠቀሙ መገኘት፣
18.2.9. ማንኛውንም የዩኒቨርሲቲውን ንብረት በአግባቡ አለመጠቀም፣ ማበላሸት፣
18.2.10. ህጋዊ ባልሆነ መንገድ በአጥር ዘሎ ወይም ሾልኮ መግባትና መውጣት፣
18.2.11. በመኝታ ክፍል ውስጥ ያልተፈቀዱ የኤሌክትሪክ እቃዎችን መጠቀም፣
18.2.12. ለዩኒቨርሲቲው መምህራን፣ ሰራተኞችና ሀላፊዎች ሥራው የሚጠይቀውን አስፈላጊውን ትብብር አለማድረግ፣
18.2.13. ህጋዊ ያልሆነ ስብሰባ ወይም በተማሪዎች ጉዳይ ዳይሬክተር ወይም በዩኒቨርሲቲው ከፍተኛ አመራር ፈቃድ ያላገኘ ትእይንት ማሳየት ወይም ለማሳየት መሞከር፣
18.2.14. የራስን ሃይማኖት፣ እምነትና የፖለቲካ አመለካከት ሌሎች እንዲቀበሉ ጫና መፍጠር፣ መረበሽ
18.2.15. በመግቢያ በርና በአገልግሎት መስጫዎች የመታወቂያ (የመገልገያ) ካርድ ሲጠየቅ ለማሣየት ፈቃደኛ አለመሆን፣
18.2.16. ሃይማኖታዊ በአሎችንና ትዕይንቶችን በግቢው ውስጥ ማካሄድ፣ እንዲካሄዱ መቀስቀስ፣ ማነሳሳት፣ መምራት፣
18.2.17. ሌሎች መሰል የስነ-ምግባር ጥፋቶችን መፈፀም፣

አንቀጽ 19፡- መካከለኛ ጥፋቶች

19.1. ማንኛውም ሰው በከፍተኛ ትምህርት ተቋም ውስጥ የአፍና አፍንጫ መሸፈኛ ማድረግ ቀሪ መሆኑ እስከሚወሰንበት እና ስልጣን ባለው አካል በይፋ እስከሚገለጽበት ጊዜ ድረስ ከመኝታ እና ከመመገቢያ ሰዓት ውጪ በማንኛውም ቦታ የአፍና አፍንጫ መሸፈኛ ሳያደርግ መንቀሳቀስ

19.2. የከፍተኛ ትምህርት ተቋም ውስጥ ተገልጋዮች በሚቀመጡበት ጊዜም ይሁን በማንኛዉም አኳኋን አገልግሎቱን ሲያገኙ ከሁለት ሜትር በታች ተጠጋግተው እና የአፍ እና አፍንጫ መሸፈኛ ሳያደርጉ አገልግሎት እንዲያገኙ ማድረግ ወይም ከተማሪዎች ምግብ ቤት ውጪ ባሉ ምግብ ቤቶች ጠረጴዛቸው በአንድ ጠረጴዛ ከሶስት ተገልጋዮች በላይ እንዲቀመጡ ማድረግ

19.3. የተቀደደ፣ በአግባቡ ያልጸዳ ወይም በአግባቡ ያልጸዳ የአፍና የአፍንጫ መሸፈኛ ማስክ ማድረግ

19.4. በተቋም ግቢ ውስጥ በሚደረግ እንቅስቃሴና የጋራ አገልግሎት በሚሰጥባቸው ቦታዎች ከሁለት ሜትር በታች ርቀት መቆምም ሆነ መቀመጥ

19.5. ከተማሪዎች ምግብ ቤት እና ከሌሎች ግቢ ውስጥ ካሉ ምግብ ቤቶች የሚወጡ ትራፊ ምግቦችን ለሌላ ለማንኛውም ግልሰብም ሆነ አካል አሳልፎ መስጠት ወይም መሸጥ

19.6. ማንኛውም የከፍተኛ ትምህርት ተቋም ማህበረሰብ አባል ተቋሙ ካለበት ከተማ ውጪ ከአቅም በላይና አሳማኝ በሆነ ምክንያት የተጓዘ እንደሆነ ቀድሞ የጉዞ ታሪኩን ተቋሙ ውስጥ ላለው ማዕከል ማስመዝገብ ያለበት ሲሆን ከጉዞ መልስ ራሱን በለይቶ ማቆያ ውስጥ ሳያቆይ በቀጥታ ከሌላው ማበህረሰብ ጋር መቀላቀል

19.7. ማንኛውም የአካል ቅርርብንና ንኪኪን የሚፈልጉ የተማሪዎች የቤት ውስጥና ከቤት ውጭ ያሉ መዝናኛዎች፣ የመዝናኛ መሳሪያዎችና ጨዋታዎች እና በማንኛውም ደረጃ የሚደረግ የቡድን ስፖርት ውድድር ማድረግ

19.8. በግል ካልሆነ በስተቀር በቡድን ስፖርታዊ እቅስቃሴ ማድረግ የተከለከለ ነው::

19.9. የስነ-ጽሑፍ ምሽቶችና የተለያዩ የመዝናኛ መሰባሰቦች ለኮቪድ-19 ስርጭት ምክንያት ስለሚሆኑ

19.10. በግቢ ውስጥ ባሉ ማንኛውም የመዝናኛ ስፍራዎች በቡድን መጫዎት

19.11. ለአንድ ወሰነ ትምህርት ከትምህርት ገበታ የሚያሳግዱ ጥፋቶች

19.11.1. ከላይ የተጠቀሱት ወይም ተመሳሳይ ጥፋት በድጋሜ ፈጽሞ መገኘት፣

19.11.2. ፈተና መስረቅ ወይም ፈተና መኮረጅ ወይም ማስኮረጅ፣ የሌላ ሰው ሥራን የራስ አስመስሎ ማቅረብ፣

19.11.3. ሴትም ሆነ ወንድ ተማሪዎችን በንግግር፣ በጽሁፍ፣ በስልክ፣ ወዘተ ማስፈራራት፣ ማስቸገር፣ ማስጨነቅ፣ መሳደብ

19.11.4. የተለጠፉ ህጋዊ ማስታወቂያዎችን መገንጠል፣ መቅደድ፣ መደለዝ ወይም ማበላሸት፣

19.11.5. በምንም ይሁን በምንም ሁኔታ ከተማሪ ጋር ጥል መፍጠር፣ ለድብደባ መጋበዝ

19.11.6. የዩኒቨርሲቲውን መምህር፣ ሰራተኛ ወይም ሌሎችን መዝለፍ፣ ማንጓጠጥ፣ መሳደብ፣ ለመምታት መጋበዝ

19.11.7. ህጋዊ ፍቃድ የሌላቸው ስብሰባዎችንና ምክክሮችን በግቢው ውስጥ ማካሄድ፣ መሳተፍ፣

19.11.8. የራስ መታወቂያ ወይም የመመገቢያ ካርድን ለሌላ አካል አሳልፎ መስጠት፣

19.11.9. በሌላ ተማሪ መታወቂያ ወይም መመገቢያ ካርድ አገልግሎት ለማግኘት ማጭበርበር፣ ሲመገቡ መገኘት

19.11.10. ለተማሪዎች የትራንስፓርት አገልግሎት ለመስጠት በሚደረገው እንቅስቃሴ በማንኛውም ስም ከተመን በላይ ማስከፈል፣ ለማስከፈል መሞከር፣ ለማስከፈል ማስተባበር መተባበር

19.11.11. የአንድን ተማሪ መታወቂያ ወይም የመመገቢያ ካርድ ወይም ሌሎች ንብረቶችን ገንዘብ ወይም ሌሎች ጥቅማ ጥቅም ለማግኘት በቅድመ ሁኔታነት መያዣ ማድረግ፣

19.11.12. በተቋሙ ውስጥ የሚካሄድ አካዳሚያዊ፣ አስተዳደራዊ፣ ማህበራዊ፣ ስፖርታዊ ወይም ሌሎች እንቅስቃሴዎችን መረበሽ ወይም ተገቢ ያልሆነ ጣልቃ ገብነት መፈጸም፤

19.12. ከአንድ ዓመት እስከ ሁለት ዓመት የሚያስቀጡ ጥፋቶች በዚህ ምድብ ይካተታሉ::

19.12.1. ሆን ብሎ የፈተና ወረቀት ሳያስረክብ ይዞ መውጣት፣ የሌላ ተማሪ የታረመም ሆነ ያልታረመ የፈተና ወረቀት ለማጥፋት መሞከር ወይም ማጥፋት ወይም መቅደድ፣

19.12.2. በፈተና ወረቀቱ ላይ ስሙን ቀይሮ እንዲፈተንለት ሌላ ዲፓርትመንት ተማሪ ወይም ተማሪ ያልሆነ ሰው በራሱ ቦታ ማስፈተን፣

19.12.3. አልኮልና ጫት ይዞ መግባት፣ ለመግባት መሞከር፣

19.12.4. መታወቂያና መመገቢያ ካርድ ሳይጠፋበት ጠፍኝ በሚል አመልክቶ ሁለተኛ ለማግኘት መሞከር ወይም አግኝቶ በሁለት ካርድ ሲጠቀም መገኘት፣

19.12.5. በቤተ መጽሐፍት ወይም በሌሎች ክፍሎች ውስጥ ያሉ መጽሐፍትን፣ ጆርናሎችን ወዘተ ገጽ መቅደድና መገንጠል፣ ወይም መስረቅ

19.12.6. መረጃ በሌለበት በአሉባልታ፣ በመሰለኝና ባልታረጋገጠ ወሬ በስብሰባዎች ላይም ይሁን በሌሎች ሁነቶች የዩኒቨርሲቲውን ኃላፊዎች፣ መምህራን፣ የአስተዳደር ሠራተኞች ወይም ሌሎች ተማሪዎችን ማቃለል፣

የሃሰት ንግግሮችን በማድረግ ና በተለያዩ ማህበራዊ ሚዲያዎች በመጻፍ ክብር መንካት፣ ስም ማጥፋትና የመሳሰሉ ድርጊቶችን መፈጽም፣

19.12.7. በዩኒቨርሲቲው ማህበረሰብ አባል ላይ የስነ-ልቦና ጉዳት ማድረስ፣ መሳደብ፣ ማስፈራራት፣ መዝለፍ፣ መረበሽ፣ ማስጨነቅ፣ እንዲሁም አእምሮውን፣ ማህበረሰባዊ ግንኙነቱን፣ ህይወቱን ወይም እንቅስቃሴውንና የስራ ሞራሉን ሊጐዱ የሚችሉ ሃይለ ቃሎችን መናገር፣ በሥራው ላይ እንቅፋት የሚሆኑ ነገሮችን ማድረግ፣

19.12.8. ሳይታመም የታመመ በማስመሰል ከክሊኒክ መድኃኒት አውጥቶ ሲሸጥ ወይም ለሌላ ሰው ሲሰጥ መገኘት፣

19.12.9. መታወቂያ ካርዱን ወይም መመገቢያ ካርዱን፣ የቤተ-መጽሐፍት መዋሻ ካርድ ወይም ሌላ የግል መለያውን ለሌላ ተማሪ አሳልፎ በመስጠት ማስጠቀም ወይም ከሌላው ተቀብሎ መጠቀም፣

19.12.10. የሌላ ተማሪ መመገቢያ ካርድ፣ መታወቂያ ወይም ሌላ ዕቃ ሰርቆ ከወሰደ በኋላ እንዲመልስ ሲጠየቅ በገንዘብ ወይም በዓይነት ጥቅም ለማግኘት መደራደር ወይም ይህን ድርጊት ከሚፈጽም ሰው ጋር መተባበር፣

19.12.11. በሆቴሎች፣ በጭፈራ ቤቶች ወይም በሌሎች ቦታዎች በሴተኛ አዳሪነት ተሰማርቶ መገኘት ወይም እነዚህን የሚመስሉ ተግባራትን መፈጸም ወይም ይህን እንዲያደርጉ መገፋፋት፣ እንደአገናኝ ማገልገል፣

19.12.12. ያለግለሰቡ ፈቃድ ምስሉን ወይም ድምጹን በካሜራ ወይም በሞባይል ቀርፆ ለህዝብ ማሳየት ወይም ማሰማት፣ ለማንኛውም ተግባር እንዲውል ማድርግ፣

19.12.13. ለተማሪዎች ህብረት ስራ ማስኬጃ የተበጀተውን ገንዘብ ወይም የተማሪዎች ክበብ በድጋፍ ያገኘውን ወይም ከአባላት የተሰበሰበውን ገንዘብ የፋይናንስ የገቢና ወጭ ስርዓት ባልተከተለ መልኩ ማስኬድ፣ መመዝበር፣

19.12.14. በተማሪዎች ህብረት አባላት ላይ ሆን ብሎ ማመጽ፣ ችግር መፍጠር፣ ማዋከብ፣ ብሔራቸውን ወይም ሌሎች ማንነታቸውን መሠረት አድርጎ ማጣጣል፣ መስደብ፣ሌሎች እንዲነሱባቸው መቀስቀስ፣ (ችግር ያለባቸውን ለይቶ በህጋዊ መንገድ እንዲነሱ በመረጃ ላይ የተደገፈ ጥያቄ ማቅረብ እንደተጠበቀ ሆኖ።)

19.12.15. በዩኒቨርሲቲ ሰራተኛ ወይም ተማሪ ላይ በማስፈራራት ወይም በመዛት የሆነ ነገር እንዲያደርግ ወይም እንዳያደርግ ማስገደድ፣

19.12.16. የዲሲፕሊን ጉዳይ የሚያይ የኮሚቴ አባልን፣ አመልካች ወይም ምስክር ሆኖ የቀረበ ሰውን፣ የተከሳሹን ወይም መከላከያ ምስክሮቹን ማስፈራራትና ውሳኔ እንዳይተላለፍ የማድረግ ሙከራ፣ ማጣራት በትክክልኛ መንገድ እንዳይካሄድ ማድረግ፣

19.12.17. ሐይማኖትን መሠረት በማድረግ ለራሱና ተከታዮቹ ልዩ መመገቢያ አዳራሽና ምግብ መጠየቅ፣ መመገቢያ አዳራሽ ውስጥ ከምግብ በፊትና በኋላ ፀሎት ሲያደርጉ ድምጽ ማሰማት፣ በቡድን ድምጽ እያሰሙ መጸለይ፣ ሌሎችን መረበሽ

19.12.18. ሐይማኖትን መሠረት በማድረግ ለራሱና ተከታዮቹ ልዩ የመመገቢያ ሰዓትና ምግብ በመጠየቅ ሁከት እንዲፈጠር ማድረግ፣

19.12.19. በተማሪዎች ህብረት አባልነት ስም ሥልጣን ያለአግባብ መጠቀም፤

19.12.20. በዩኒቨርሲቲው በሚሰጡ ፈተናዎች ለሌላ ተፈታኝ ተማሪ ወይም አካል ሲፈተን መገኘት፣

19.12.21. የሌሎችን የፖለቲካ፣ የኃይማኖት፣ ብሄር፣ ቋንቋ፣ አመለካከት፣ ባህልና እምነት ማንቋሸሽ፣ ማንኳሰስ፣ የሃይማኖት መጽሐፍት ማበላሸት፣ ማቃጠል፣ የበዓላት ቀናትን አሳብቆ መረበሽ፣ ወዘተ፣

19.12.22. በሌሎች ተማሪዎች ወይም የዩኒቨርሲቲው ማህበረሰብ አባላት ላይ የሞራል ችግር ሊያስከትሉ የሚችሉ ትዕይንቶችን፣ እንቅስቃሴዎችን፣ ፊልሞችንና የመሳሰሉ ነገሮችን ማሳየት፣ ማቀነባበር ወይም ማሰራጨት፣

19.12.23. ሌሎች በዚህ ምድብ ሊካተቱ የሚችሉ ጥፋቶች ተብለው በዩኒቨርሲቲው በጽሑፍ የሚለዩ ጥፋቶችን መፈጸም ፣

አንቀጽ 20፡- ከፍተኛ ጥፋቶች

20.1. ማንኛውም ሰው በከፍተኛ ትምህርት ተቋም ውስጥ ለሰላምታና ለሌላ ለማንኛውም አላማ በእጅ መጨባበጥ፣ የእርስ በእርስ አካላዊ ንክኪ ማድረግ

20.2. ኮቪድ-19ን ለመከላከል የሚደረጉ የጥንቃቄ መልዕክቶችን ይዘው የተለጠፉት ማስታወቂያዎችን መቅደድ፣ ሌላ ማስታወቂያ ደርቦ መለጠፍ፣ ማበላሸት ወይም በሌላ ቁስ መጋረድ

20.3. በመማሪያ ክፍሎች እና በምግብ ቤት አዳራሾች እንዲሁም በመዝናኛና በክሊኒክ ቦታዎች በምንም መልኩ ያልተገባ ጩኸት፣ ጠብ፣ ግርግር መፍጠር፣ መረበሽ

20.4. በአገልግሎት ዙሪያ ቅሬታ ሲኖር ሰላማዊ እና ሕጋዊ መንገድን ተከትሎ መጠየቅ ሲቻል አመፅ ማንሳት፣ ማስነሳትና መተባበር

20.5. ተማሪ ያልሆነ ወይም የተባረረ ተማሪን በተማሪዎች መኝታ ቤት ማሳደር ወይም ማኖር፣

20.6. በተቋማት ላይ የተጣሉ ግዴታዎችን አለመወጣት (ይህ በየደረጃው ባለው አመራር ላይ የሚቆጠር ጥፋት ነው)

20.7. የዩኒቨርሲቲውን ህግና ደንብ ለመጣስ፣ የአሰራር ስርአትና የሥራ አመራር ውሳኔ ለመቃዎም ተማሪዎችን ለአድማ፣ ለአመጽና ለረብሻ ማነሳሳት፣ ማስተባበር፣ የሃሰት ወሬ መፍጠርና የተለያዩ ሚዲያዎችን በመጠቀም ማስፋፋት፣ ለህገ-ወጥ ሥራ ህብረት መፍጠር፣

20.8. በማስታወቂያ ሰሌዳዎች ላይና በሌላ ቦታ ብጥብጥና ሁከት የሚያስከትል ያልተፈቀዱ ጽሁፎችን መለጠፍ፣

20.9. በአግባቡ በመካሄድ ላይ ባለ የዲሲፕሊን ጥፋት ክርክር የመሰማት ሂደት ላይ ጣልቃ መግባትና ማደናቀፍ፣ በስርዓቱ መሠረት ለመዳኘት የሚያመለክቱ ተማሪዎችንና ሠራተኞችን ማደናቀፍ፣ በዲስፕሊን ኮሚቴዎች ላይ ወከባ በመፍጠር በገለልተኝነታቸው ላይ ተፅዕኖ ለመፍጠር መሞከር፣

20.10. እንደ ማሪዋና፣ ካናቢስ፣ ሀሽሽ፣ ኮኬይን ወዘተ ያሉ ዕፆችን መጠቀም፤ በዩኒቨርሲቲው ግቢ ውስጥ ውስጥም ሆነ ከዚያ ውጭ ይዞ መገኘት ወይም በድብቅ ሲያዘዋውር ወይም ሲሸጥ መገኘት፣

20.11. ተማሪው የፖለቲካ ወይም የብሔር ምክንያቶችን በማንሳት ተገቢ ባልሆነ መንገድ ሰዎችን ለአመጽ ማነሳሳት፣

20.12. ሆን ብሎ የሌላ ተማሪን የስራ ውጤት መደበቅ ወይም ማጥፋት

20.13. ገንዘብ ወይም ሌላ ዋጋ የሚያወጣ ነገር በመስጠት ያልተገባ የትምህርት ጥቅም ለማግኘት መሞከር፣

20.14. በዩኒቨርሲቲው ቅጥር ግቢ ውስጥ በህዝብ ፊት ራቁትን መታየት፣

20.15. ዩኒቨርሲቲው በሚያወጣቸው ሕጎች ተገዢ ለመሆን አለመፈለግ፣ ያለበቂ ምክንያት የትምህርትና ስልጠና ፕሮግራሞች እንዲቀየሩ አመጽ ማስነሳት፣ ሰላምን ማወክ፣ በተደጋጋሚ እንደማይለወጡ ተነገሮ ለመቀበል ዝግጁ አለመሆን፣

20.16. ማንኛውም የትምህርትና ሥልጠና ተቋም ማኅበረሰብ አባል በግልም ሆነ በቡድን በማንኛውም መልኩ የተቋሙን ሠላማዊ የመማር ማስተማር ሂደት የሚያውክ እንቅስቃሴና ተግባራትን ማቀድ፣ መፈጸም፣ ማስተባበር፣ መተባበር የተከለከለ ነው፡፡

20.17. ማንኛውም የትምህርትና ሥልጠና ተቋም ማኅበረሰብ አባል በግልም ሆነ በቡድን ፖለቲካ፣ ኃይማኖት ወይም ብሔር ተኮር የግጭት መንስኤና አባባሽ የሆኑ፣ አለመግባበትና ጥርጣሬ የሚፈጥሩ እንቅስቃሴዎችና ተግባራትን መፈጸም የተከለከለ ነው፡፡

አንቀጽ 21፡- በጣም ከፍተኛ ጥፋቶች

21.1. ከፍተኛ የዲስፕሊን ጥፋቶችን ፈጽሞ በተወሰደው እርምጃ መሻሻል ሳያሳይ ለሁለተኛ ጊዜ ጥፋት ፈፅሞ መገኘት፣

21.2. ማንኛውም የከፍተኛ ትምህርት ተቋም የፊት ለፊት ትምህርት መስጠት መጀመር እንደሚችል ከሚመለከተው አካል ቅድመ ሁኔታዎች የተሟሉ ስለመሆኑ ተረጋግጦ ውሳኔ/ፈቃድ ሳይሰጥ እንዲሁም አጠቃላይ የመማር ማስተማር ስራውን በተመለከተ የሚደረጉ የጥንቃቄ እርምጃዎችን ሳያከብር ወይም ሳይከተል ትምህርት መስጠት

21.3. ማንኛውም ሰው በከፍተኛ ትምህርት ተቋም ውስጥ ኮቪድ-19 እንዳለበት እያወቀ ወደ ከፍተኛ ትምህርትና ስልጠና ተቋም ውስጥ መግባት፣ ከተቋሙ ማህበረሰብ ጋር መቀላቀል ወይም ቫይረሱ ወደ ሌሎች ሰዎች ሊተላለፍ በሚችልበት ሁኔታ ከሌሎች ከከፍተኛ ትምህርት ተቋማት ማህበረሰብ አባላት ጋር መገናኘት ወይም በሀሰት ቫይረሱ እንዳለበት/እንዳለባት አድርጎ ማስመሰል

21.4. ማንኛውንም ተቋሙንና የተቋሙን ማህበረሰብ አባላት የተመለከተ የኮቪድ-19 መረጃ ሳይፈቀድለት በተለያዩ መንገዶች መግለጽ

21.5. ሰላማዊ የመማር ማስተማርን ለማወክ ማቀድ ወይም ማስተባበር ወይም መተግበር ወይም መተባበር

21.6. በግቢ ውስጥ በቡድን ሆኖ ማንኛውንም ዓይነት ኃይማኖታዊም ይሁን ፓለቲካዊ እንቅስቃሴ ማድረግ

21.7. ሃይማኖትን፣ ብሔርን፣ ባህልንና ቋንቋን የሚያንቋሽሽ ማንኛውንም ንግግር ማድረግ፤ መጻፍ ወይም ድርጊት መፈጸም

21.8. ወደ ግቢ ውስጥ ማንኛውም ዓይነት አደንዘዥ እፅ ማዛወር፣ ማብቀል/መትከል፣
21.9. የትምህርና ስልጠና ማህበረሰብ አባል በምንም ሁኔታ መሳደብ፣ መዝለፍ፣ ማንጓጠጥ፣ ማስፈራራትና መዛት፣ ያልተገባና ፀያፍ ንግግር መናገር
21.10. በግቢው ውስጥ በግልም ሆነ በቡድን ፀብ ማንሳት ወይም መደባደብ ወይም በነዚህ መሠል ተግባራ መተባበር
21.11. የስርቆትና የሙስና ተግባር መፈጸም፤
21.12. በብሔር ወይም በኃይማኖት ወይም በትውውቅ አድሎ መፈፀም
21.13. የሌሎችን ብሔር ወይም ኃይማኖት የሚጎዳ ድርጊት መፈፀም ለምሳሌ፡- መንፈሳዊ መጽሐፍት፣ ስዕሎችና ቅርፃቅርፆች፣ ሐይማኖታዊ ምልክቶች እንዲቃጠሉ ወይም ቅርፃቸው እንዲጠፋ ማድረግ፣
21.14. ድምጽ ባለው ወይም በሌለው መሣሪያ የዩኒቨርሲቲውን ማህበረሰብ አባል ሆነ ከዩኒቨርሲቲው ውጭ ያሉ የማህበረሰብ አባላትን መጉዳት ወይም ለመጉዳት ሙከራ ማድረግ፣
21.15. በዩኒቨርሲቲው ቅጥር ግቢ ውስጥ የአካል ጉዳት ወይም ሞት ሊያስከትሉ የሚችሉ ስለታማና ተተኳሽ መሳሪያዎች ወይም መርዛማ ነገሮችን ይዞ መገኘት፣ ለመግባት መሞከር
21.16. አስገድዶ መድፈር ወይም የተቃራኒ ፆታውን የመከላከል አቅም በጉልበት ወይም በስነ-ልቦና ጫና በማድከም ፆታዊ ጥቃት ማድረስ ወይም ለማድረስ መሞከር፣ በጉልበት ገፍቶ ወደ ተቃራኒ ፆታ መኝታ ቤት መግባት፣፣
21.17. በዩኒቨርሲቲው ቅጥር ግቢ ውስጥ ሆን ብሎ ወይም በቸለልተኛነት ወይም በጥንቃቄ ጉድለት ቃጠሎ ለማስነሳት መሞከር ወይም ማስነሳት፣
21.18. በተጭበረበረ የትምህርት ማስረጃ ተመዝግቦ መገኘት፣
21.19. ፊርማን መኮረጅ ወይም ሰነድን መደለዝ፣ በመሰረዝ ማጭበርበር፣ ለማጭበርበር መሞከር፣
21.20. በማስፈራራትና ጉልበት በመጠቀም የሌላ የተቋሙን ማህበረሰብ አባል ንብረት መውሰድ ወይም ለመውሰድ ሙከራ ማካሄድ (ዘረፋ መፈፀም)፣
21.21. ተገቢውን ክፍያ ሳይፈጽም ወይም የወጭ መጋራት ውል ሳይፈርም መማር ወይም የአገልግሎት ተጠቃሚ ለመሆን መሞከር፣
21.22. የሌላ ተማሪን ቋንቋ፣ ብሔር፣ ሐይማኖት እና ማንነት ማንቋሸሽ፣
21.23. ተማሪው ባገኘው ውጤት ወይም ሠራተኛው በተሰጠው የሥራ አፈጻጸም ውጤት ቅር በመሰኘት በመዛኙና በመዛኙ ቤተሰብ ላይ ጉዳት ለማድረስ መሞከር ወይም ማድረስ፣
21.24. በመመገቢያ አዳራሽ አካባቢ ከምግብ ጋር አያይዞ ወይም በየትኛውም ምክንያት ዓመጽ ማስነሳት ወይም ለማስነሳት መሞከር፣ በስራ ላይ ያሉ ስራተኞችን መደባደብ፣
21.25. ሌሎች ከነዚህ ጋር ይመሳሰላሉ ብሎ ተቋሙ በጽሑፍ የሚጨምራቸው ጥፋቶች

ክፍል ስምንት
የዲስፕሊን ኮሚቴ

አንቀጽ 22፡- የዲስፕሊን ኮሚቴ ስለማቋቋም

የተማሪዎችና የሠራተኞች (መምህራንና አስተዳደር ሠራተኛ) ዲስፕሊን ኮሚቴ በተቋም ደረጃ እና በከምፓስ ደረጃ ጸንተው ባሉ ህጎች መሠረት በተቋሙ የበላይ ኃላፊ የሚቋቋም ነው፡፡

አንቀጽ 23፡- የዲስፕሊን ኮሚቴው ተጠሪነት

ሀ. በተቋም ደረጃ ያለ የዲስፕሊን ኮሚቴ አስተዳደር ዘርፍን ለሚመራ ምክትል የተቋም ኃላፊ ተጠሪ ይሆናል፡፡
ለ. በከምፓስ ደረጃ ያለ የዲስፕሊን ኮሚቴ ተጠሪነቱ ለከምፓሱ ኃላፊ ይሆናል፡፡
ሐ. ስለሆነም ኮሚቴው ማንኛውንም የዲስፕሊን የውሳኔ ሐሳብ ተጠሪ ለሆኑበት አካላት በማቅረብ ያስጸድቃል፡፡

አንቀጽ 24፡- የተማሪዎች የዲስፕሊን ኮሚቴ አባላት

ስብጥሩም ከመምህራን፣ ከተማሪዎች ህብረትና እንደአስፈላጊነቱ ከአስተዳደር ሠራተኞች የተውጣጡ አባላት ያሉት ይሆናል።

24.1. የተማሪዎች የዲስፕሊን ኮሚቴ አምስት አባላት ይኖሩታል፡፡ እነርሱም፡-

ሀ. አንድ ነባር መምህር .....ሰብሳቢ (በተቋሙ የበላይ ኃላፊ የሚሰየም)

ለ. ሁለት የተማሪዎች ህብረት ተወካዮች (አንድ ወንድና አንድ ሴት.....አባል (በተማሪዎች ህብረት ስራ አስፈጻሚ የሚወከል)

ሐ. የመምህራን ማህበር ተወካይ.....አባል (በመምህራን ማህበር ሰብሳቢ ወይም ም/ሰብሳቢ)

መ. አንድ የአስተዳደር ሠራተኛ.....አባልና ፀሐፊ (በተቋሙ የበላይ ኃላፊ የሚሰየም)

24.2. የሠራተኞች የዲስፕሊን ኮሚቴ አምስት አባላት ይኖሩታል፡፡

እነርሱም፡-

ሀ. አንድ ነባር መምህር .....ሰብሳቢ (በተቋሙ የበላይ ኃላፊ የሚሰየም)

ለ. የሴቶች፣ ህጻናትና ወጣቶች ዳይሬክተር.....አባል

ሐ. የመምህራን ማህበር ተወካይ-.....አባል (በመምህራን የሚወከል)

መ. የአስተዳደር ሠራተኞች ተወካይ .....አባል (በሠራተኞች የሚወከል)

ሠ. አንድ ነባር የአስተዳደር ሠራተኛ .....አባልና ፀሐፊ (በተቋሙ የበላይ ኃላፊ የሚሰየም)

አንቀጽ 25፡- የዲስፕሊን ኮሚቴ አባላት የሚከተሉትን ሊያሟሉ ይገባል፤

ሀ. በተቋሙ ውስጥ በስነ-ስርዓት አከባሪነታቸው፣ በታማኝነታቸውና በቁርጠኝነታቸው የሚታወቁና ፍትሃዊና ሚዛናዊ እይታ ያላቸው፤ የማያዳሉ፤

ለ. በዲስፕሊን ጥፋት ተከሰውና ተቀጥተው የማያውቁ

ሐ. በተቋሙ ውስጥ በአብዛኛው ወገን ተቀባይነት ያላቸው

መ. በተቋሙ ቢያንስ የአንድ ዓመት ቆይታ ያላቸው

ሠ. ከላይ ከ(ሀ) እስከ (መ) የተገለጸው እንደተጠበቀ ሆኖ አዲስ ተቋም/ካምፓስ ሲቋቋም የተቋሙ የበላይ ኃላፊ የሚወስን ይሆናል፡፡

አንቀጽ 26፡- የኮሚቴው ሥልጣን

ሀ. ኮሚቴው የቀረበለትን የዲስፕሊን ጥፋት ክስ በዚህ መመሪያ መሠረትና ሌሎች በተቋሙና በተቋሙ ማህበረሰብ ላይ ተፈፃሚነት ካላቸው ህጎች ጋር በማገናዘብ መርምሮ የውሳኔ ሐሳብ ያቀርባል፡፡

ለ. የዲስፕሊን ኮሚቴ በይግባኝ የቀረበ ከሆነ መርምሮ የውሳኔ ሃሳቡን ለአስተዳደር ዘርፍ ምክትል ኃላፊ ያቀርባል፡፡

ሐ. ክሱን በሚመለከት ከጉዳዩ ጋር በተያያዘ ማንኛውንም የሥራ ክፍል መረጃው ጠይቆ የመውሰድ፣ ማንኛውንም አካል አስቀርቦ የመመርመር ሥልጣን ይኖረዋል፡፡ የሥራ ክፍሎችም የመተባበር ግዴታ አለባቸው፡፡

አንቀጽ 27፡- የኮሚቴው አባላት መጓደል

ከኮሚቴው ውስጥ አንድ አባል የተጓደለ ከሆነ የተቋሙ የበላይ ኃላፊ እንዲያውቀው ተደርጎ በኮሚቴው ሰብሳቢ አቅራቢነት ተጠሪ የሆኑበት የቅርብ ኃላፊ ተተኪ ይመድባል፡፡ ከአንድ በላይ አባል ከሆነ ግን የኮሚቴ አሰየየምን ተከትሎ ይፈጸማል፡፡

አንቀጽ 28፡- ከኮሚቴ አባልነት ስለመነሳት

ሀ. የኮሚቴው ሰብሳቢ ከሳሽ በሚሆንበት ጊዜ በአባላቱ ውሳኔ መሠረት ከአባላቱ መካከል አንዱ ሰብሳቢ ይሆናል፡፡

ለ. የኮሚቴው ሰብሳቢ ወይም ማንኛውም አባል ክስ ከቀረበበት ግለሰብ ጋር የግል ጠብ ወይም የስጋ ወይም የጋብቻ ዝምድና ያለው መሆኑ ሲረጋገጥ ለዚህ ጉዳይ ብቻ በጊዜያዊነት ከሰብሳቢነቱ ወይም ከአባልነቱ እንዲነሳ ይደረጋል።

ሐ. ማንኛውም የኮሚቴ አባል ራሱን ከጉዳይ በማግለል በሌላው አባል ላይ ተጽእኖ ለመፍጠር ወይም ችግር ውስጥ ለማስገባት ከባለጉዳይ ጋር እየተገናኘ ሚስጢር ያወጣ ወይም ቃለ ጉባኤዎችን፣ መረጃዎችንና ጽሁፎችን ለባለጉዳይ ያሳየ ወይም የገለጸ ወይም የሰጠ እንደሆነ ከአባልነቱ ይነሳል፣ በከፍተኛ የዲስፒሊን ጥፋትም በአባላቱ ወይም በሰብሳቢው ይከሰሳል፤ አስፈላጊው አስተዳደራዊ እርምጃ ይወሰዳል።

መ. ማንኛውም የኮሚቴ አባል በተደጋጋሚ ያለ ማንም ፈቃድ የኮሚቴ ስብሰባ ጥሪ ሲደረግ የሚቀር ከሆነ የጽሑፍ ማብራሪያ እንዲያቀርብ ይደረጋል፤ ጉዳዩም በፋይሉ ውስጥ እንዲያያዝ ይደርግና ከአባልነቱ እንዲነሳ ይደረጋል፡፡ በዲስፕሊን ጥፋትም ሊጠየቅ ይችላል፡፡

አንቀጽ 29፡- የኮሚቴው ምልዓተ ጉባኤና ድምጽ አሰጣጥ፣

ሀ. በኮሚቴው ስብሰባ ላይ ግማሽ (50%) አባላት ከተገኙ ምልዓተ ጉባኤው ሙሉ ይሆናል፡፡

ለ. አከራካሪ ጉዳይ ሲያጋጥም የኮሚቴው አስተያየት የሚያልፈው በድምጽ ብልጫ ሲሆን እኩል በኩል ከሆነ ሰብሳቢው ባለበት ወገን የቀረበው ሃሳብ ይፀድቃል፤ በሃሳብ የተለየ አባል ካለ የተለየበት ምክንያት በቃለ ጉባኤው ላይ ይሰፍራል፡፡

ሐ. ሰብሳቢው የክስ ሂደቱን በአግባቡ መምራት አለበት፡፡ በክርክሩ ወቅት አንድ የኮሚቴ አባል የስነ-ምግባር ግድፈት ካሳየ ከስብሰባው በጊዜያዊነት እንዲወጣ ማድረግ ይችላል፡፡ ይህ ምልዓተ ጉባኤውን ሊያጎል የሚችል ከሆነ አስተዳደር ዘርፍ ም/ኃላፊ እንዲያውቀው በማድረግ የጎደለው አባል እንዲተካ ወይም ባሉት አባላት ውሳኔ እንዲሰጥ ሊፈቅድ ይችላል፡፡

መ. ማንኛውም የኮሚቴው አባል በስብሰባው ኖረም አልኖረም የሃሳብ ልዩነት ኖረውም አልኖረውም በቃለ ጉባኤው ላይ ይፈርማል፣

አንቀጽ 30፡- የኮሚቴው የስብሰባ ጊዜና የአባላት ሰዓት አከባበር

ሀ. ኮሚቴው የሚሰበሰብበትን ቀንና ሰዓት እንደየክሱ ጉዳይ አንገብጋቢነትና ብዛት እየታየ በኮሚቴው ሰብሳቢ ይወሰናል፡፡ ቢያንስ ከአንድ ቀን በፊትም ለአባላቱ አመቺ በሆነ መንገድ የሚገለጽ ይሆናል፡፡

ለ. ማንኛውም የኮሚቴው አባል አስቀድሞ ሰብሰቢውን ሳያስፈቅድ፣ አሳማኝ ባልሆነ ሰበብ አስባብ ለተደጋጋሚ ቀናት ቢቀር ወይም ስብሰባውን ቢያስተጓጉል ሰብሳቢው በሚያቀርበው ማስረጃ መሠረት በአስተዳደር ዘርፍ ም/ኃላፊ በኩል ተገቢው አስተዳደራዊ እርምጃ ይወሰድበታል፡፡

አንቀጽ 31፡- የዲስፕሊን ኮሚቴው የስራ ዘመን

የኮሚቴው የስራ ዘመን ሁለት ዓመት ይሆናል፡፡ ሆኖም አባላት እንደገና ተመርጠው ለሁለት ዙር ብቻ ሊያገለግሉ ይችላሉ፡፡

ክፍል ዘጠኝ
የሥነ-ሰርዓት ድንጋጌዎች

አንቀጽ 32፡-የዲስፕሊን ጥፋት ክስ አመሠራረት

1. ማንኛውም ከመማር ማስተማር ጋር የተያያዙ ጥፋቶችን ተፈጽመው ሲገኙ ግለሰቡ (ተማሪ፣ መምህር፣ አስተዳደር ሠራተኛ) አባል ሆኖ ያለበት የትምህርት ክፍል ኃላፊ ወይም የሥራ ክፍል ኃላፊ በጽሑፍ የተደራጀ ክስ ይመሰርታል፡፡ ይህም ከምዘናና ከፈተና አስተዳደር፣ ከቤተ መጽሐፍት፣ ከሪጅስትራር፣ ከመማሪያ ክፍል፣ ከዩኒቨርሲቲ ውስጥና ከዩኒቨርሲቲ ውጭ ባሉ ቤተ ሙከራዎች፣ በመስክ ላይ በሚደረግ የተግባር ትምህርትና ልምምድ፣ ከዩኒቨርሲቲ-ኢንዱስትሪ ትስስር፣ ከመምህራን፣ ከወርክሾፕና ከላቦራቶሪ ሠራተኞች ጋር በተገናኘ እና መሠል ከመማር ማስተማሩ ጋር ተያያዥ የሆኑ ዲስፕሊን ጥፋቶችን ያካትታል፡፡
2. ከላይ በንዑስ አንቀጽ (1) ከተጠቀሱት ውጭ ያሉት ማንኛቸውም ጥፋቶች በተማሪዎች ተፈጽመው ሲገኙ አስተዳደራዊ ጉዳዮች ተደርገው ተወስደው የተማሪዎች ጉዳይ ዳይሬክተር ክስ ይመሰርታል፡፡
3. ከላይ በንዑስ አንቀጽ (1) ከተጠቀሱት ውጭ ያሉት ማንኛቸውም ጥፋቶች በመምህራን ወይም በአስተዳደር ሠራተኞች ተፈጽመው ሲገኙ በሰው ሀብት ልማትና አስተዳደር ዳይክተር ክስ ይመሰርታል፡፡

አንቀጽ 33፡- የዲስፕሊን ጥፋት ክስ አቀራረብ

ማንኛውም የዲስፕሊን ጥፋት ክስ የሚከተሉትን ድንጋጌዎች ተከትሎ ይቀርባል፡፡

1. ማንኛውም የዲስፕሊን ጥፋት ክስ በጽሑፍ ይቀርባል።
2. የዲስፕሊን ጥፋት የክስ ጽሑፍ የሚከተሉትን ማካተት አለበት፡፡

ሀ. የከሳሹን ስም፣ ፊርማና አድራሻ እንዲሁም ክሱ የተመሰረተበት ቀን

ለ. የተከሳሽ ስም፣ የሥራ ክፍል፣ መታወቂያ ቁጥር፣ የትምህርት ዓመት (ለተማሪ)

ሐ. የዲስፕሊን ጥፋቱ የተፈፀመበትን ቦታ፣ ቀንና ሰዓት

መ. የዲስፕሊን ጥፋቱን ዝርዝር ማብራሪያ

ሠ. የተከሰሰበት የዲስፕሊን ጥፋቱ ደረጃ

ረ. የማስረጃዎች ዝርዝር (ምስክር/እማኝ ካለ ስምና አድራሻ እንዲሁም የጽሑፍ) ከዋናው ጋር የተመሳከረ ቅጂ በማያያዝ

ሰ. ሌላ ተጨማሪ ማስረጃ (ካለ)

ረ. ተከሳሹ ከአንድ በላይ በሆነ የዲስፕሊን ጥፋት የተከሰሰ ከሆነ ለእያንዳንዱ ጥፋት ተለይቶ ከላይ (ሀ)- (ሰ) በተመለከተው መሠረት መቅረብ አለበት፡፡

ሸ. በጋራ እና ተመሳሳይ ጥፋት የተሳተፈ ከሆነ በጣምራ ሊከሰሱ ይችላሉ፡፡

አንቀጽ 34፡- ክስ መመስረቻ ጊዜ

ሀ. የዲስፕሊን ጥፋቱ ከተፈፀመበት ቀን አንስቶ በ5 የሥራ ቀናት ውስጥ መቅረብ አለበት፤

ለ. የዲስፕሊን ጥፋቱ አነስተኛ ከሆነና ለዲስፕሊን ኮሚቴ መቅረብ የሌለበት ከሆነ ሥልጣን የተሰጠው አካል ጥሰቱ በተፈጸመ በ3 ተከታታይ የሥራ ቀናት ውስጥ እርምጃ ወስዶ ያሳውቃል፡፡

ሐ. ከላይ በ(ሀ)ና በ(ለ) የተደነገገው ቢኖርም በዚህ መሠረት ያልተፈጸመ ከሆነ ጉዳዩ የሚመለከታቸው የተቋሙ ኃላፊዎች ተጠያቂነት እንደተጠበቀ ሆኖ የተቋሙ የበላይ ኃላፊዎች በየትኛውም ጊዜ ጉዳዩን ማንቀሳቀስ ይችላሉ፡፡

አንቀጽ 35፡- ክስን ስለማሻሻል

ሀ. በዲስፕሊን ጥፋት የክስ ጽሁፍ ውስጥ የተገለጸው ጥፋት ዝርዝር በሚመለከት መሠረታዊ በሆኑ ነጥቦች ላይ ስህተት ወይም ግድፈት መኖሩ ሲታወቅ የውሳኔ ሐሳብ ከመቅረቡ በፊት በማናቸውም ጊዜ ክሱን ማሻሻል ይቻላል፡፡

ለ. በንዑስ አንቀጽ (ሀ) መሠረት የዲስፕሊን ክሱ ሊሻሻል የሚችለው በከሳሹ አነሳሽነት ወይም ክሱን በሚያጣራው የዲስፕሊን ኮሚቴ ጥያቄ መሠረት ሊሆን ይችላል፡፡

አንቀጽ 36፡- ክስ ስለማቋረጥ

ሀ. የዲስፕሊን ጥፋት ክስ የቀረበበት ተከሳሽ በሞት ወይም በማናቸውም ሌላ ምክንያት ከተቋሙ ጋር ያለው ግንኙነት ሙሉ በሙሉ የተቋረጠ እንደሆነ ክሱ መታየት ያቆማል፡

ለ. ነገር ግን መካከለኛና ከዚያ በላይ የዲስፕሊን ጥፋት የፈጸመ ተከሳሽ በንዑስ አንቀጽ (ሀ) ላይ የተጠቀሰው እንደተጠበቀ ሆኖ በማንኛውም የትምህርትና ስልጠና ተቋም ለመማር የተመዘገበ ከሆነ ወይም የተቀጠረ ከሆነ ክሱ መታየቱን ይቀጥላል፡፡ ውሳኔውም ለመማር ወደተመዘገበበት ወይም ለመስራት ወደተቀጠረበት አዲሱ ተቋም ለአፈጻጸም ይላካል፡፡ ውሳኔውን የሚፈጽም ተቋም በዚህ መመሪያ መሠረት ውሳኔውን ያስፈጽማል፤ ያልተረዳው የግንዛቤ ጉዳይ ካለ ውሳኔውን ያሳለፈውን ተቋም ማብራሪያ ሊጠይቅ ይችላል፡፡

ሐ. ከውሳኔ በፊት የዲስፕሊን ክስ የተመሠረተበት ተከሳሽ ዝውውር አይፈቀድም፡፡

አንቀጽ 37፡- ክስን ስለማሳወቅ

ሀ. የዲስፕሊን ኮሚቴ ክስ የቀረበበት ተከሳሽ መልሱን ይዞ እንዲቀርብ የክሱን ጽሑፍና ማስረጃዎች ቅጅ አባሪ በማድረግ የክስ ማስታወቂያ አስፈርሞ ይሰጠዋል፡፡

ለ. የክስ ማስታወቂያው ክሱ የሚሰማበትን ቦታ፣ ቀንና ሰዓት የሚገልጽ ሆኖ ክሱ ከሚሰማበት ቀን ቢያንስ ከሶስት የሥራ ቀናት በፊት ለተከሳሹ መድረስ አለበት፡፡

ሐ. ተከሳሹ ሊገኝ ባለመቻሉ ወይም ለመቀበል ፈቃደኛ ባለመሆኑ የክስ ማስታወቂያውን ለመስጠት ያልተቻለ እንደሆነ በግልጽ በሚታይ የተቋሙ የማስታወቂያ ሰሌዳ ላይ ተለጥፎ ለአምስት ተከታታይ ቀናት እንዲቆይ ይደረጋል፡፡

አንቀጽ 38፡- የክስ መልስ ስለማቅረብ

ሀ. ተከሳሽ የክስ መልሱን ማቅረብ ያለበት በጽሑፍ ነው፡፡

ለ. ተከሳሽ የተከሰሰበት ጉዳይ፡-

1. በዲስፕሊን ጥፋት የማያስከስሰው ከሆነ ወይም
2. ቀደም ሲል ውሳኔ የተሰጠበት ከሆነ ክሱ ሊታይ አይገባውም የሚል የክስ መቃወሚያ የማቅረብ መብት አለው፡ ፡
3. ከላይ (1) እና (2) መሠረት የቀረበውን መቃወሚ የዲስፕሊን ኮሚቴው የተቀበለው እንደሆነ ክሱ እንዲቋረጥ የውሳኔ ሀሳብ ያቀርባል፡፡ መቃወሚያውን ያልተቀበለው ከሆነ በዲስፕሊን ጥፋት የተከሰሰው ተከሳሽ ለቀረበበት ክስ መልስ እንዲሰጥ ያዘዋል፡፡

ሐ. የዲስፕሊን ክስ የቀረበበት ተከሳሽ ክሱን በማመን ወይም በመካድ መልሱን ማቅረብና ሲጠራም በአካል በመቅረብ ለዲስፕሊን ኮሚቴው ስለጉዳዩ የማስረዳት ግዴታ አለበት፡፡

መ. የክስ መልሱ በክሱ ለተጠቀሰው ለእያንዳንዱ የዲስፕሊን ጥፋት የተሰጠውን ምላሽና ተከሳሹ የሚፈልጋቸውን የመከላከያ ማስረጃዎችን ዝርዝር የያዘ ሊሆን ይገባል፡፡

ሠ. የክስ መልሱ ተከሳሽ ከዘረዘራቸው የመከላከያ ማስረጃዎች መካከል በእጁ የሚገኙትን የጽሑፍ ማስረጃዎችን ቅጅ የያዘና የዲስፕሊን ኮሚቴው እንዲያስቀርብለት የሚጠይቃቸውን ማስረጃዎች የትና በማን እጅ እንዳሉ በግልጽ የሚያሳይ መሆን አለበት፡፡

ረ. በዲስፕሊን የተከሰሰ ተከሳሽ የመከላከያ ማስረጃዎችን አቅርቦ የማሰማት መብት ይኖረዋል፡፡ ነገር ግን ቅረብ በተባለበት ዕለትና ሰዓት ባይቀርብ በቀረቡት ሪፖርቶችና ማስረጃዎች ላይ መሰረት ተደርጎ የቅጣት ውሳኔ ይተላለፍበታል፡፡

ሰ. በዲስፕሊን ጥፋት የተከሰሰው ተከሳሽ በማመን መልስ የሰጠ እንደሆነ ተጨማሪ ማጣራት አስፈላጊ ሆኖ ካልተገኘ በስተቀር ክሱን ከዚህ መመሪያ ጋር በማገናዘብ የውሳኔ ሐሳብ ይቀርባል፡፡

ሸ. በዲስፕሊን ጥፋት የተከሰሰው ተከሳሽ በመካድ መልስ የሰጠ እንደሆነ ኮሚቴው የሁለቱንም ወገን ምስክሮች በመስማትና ሌሎች ማስረጃዎችን በመመርመር አጣርቶ የውሳኔ ሐሳቡን ያቀርባል፡፡

አንቀጽ 39፡-ምስክር ስለመጥራት

ሀ. የዲስፕሊን ኮሚቴው ምስክሮች ከሚፈለጉበት አንድ ቀን ቀደም ብሎ ቀርበው ቃላቸውን እንዲሰጡ መጥሪያ እንዲደርሳቸው ያደርጋል፡፡

ለ. በአንድ የዲስፕሊን ጥሰት ላይ የሚመሰክሩ ምስክሮች በአንድ ጊዜ ተጠርተው ተራ በተራ በኮሚቴው ፊት ቀርበው እንዲመሰክሩ ይደረጋል፡፡

ሐ. አስፈላጊ ሆኖ ሲገኝ ተጨማሪ ምስክሮችን ከሳሹ ወይም ኮሚቴው ሊያቀርቡና ምስክርነታቸውም ሊሰማ ይችላል፡፡

አንቀጽ 40፡- የምስክር ቃል ስለመስማት

ሀ. ምስክሮች ሲሰሙ በዲስፕሊን ጥፋት የተከሰሰው ተከሳሽና ክሱን ያቀረበው አካል ሁለቱም በተገኙበት ይሆናል፡፡ ሆኖም ግን አንዱ ወገን ተነግሮት የቀረ እንደሆነ የምስክሮቹን ቃል ከመቀበል አያግድም፡፡

ለ. የምስክሮቹ መልስ ቃል በቃል የሚመዘገብ ይሆናል፡፡

ሐ. ተከራካሪ ወገኖች የቀረቡ ምስክሮችን ተጨማሪ ወይም መስቀለኛ ጥያቄዎችን መጠየቅና ይህም እንዲመዘገብላቸው ማድረግ ይችላሉ፡፡

አንቀጽ 41፡- በዲስፕሊን ጥፋት የተከሰሰው ተከሳሽ የመጨረሻ ቃል

የዲስፕሊን ኮሚቴው የዲስፕሊን ጥፋቱን የማጣራት ሥራ ከማጠናቀቁ በፊት ተከሳሹ የመጨረሻ ሐሳቡን በተከሰሰበት ጉዳይ ላይ እንዲናገር ዕድል ይሰጠዋል፡፡ ይህም ቃል በቃል ይመዘገባል፡፡ በቅጣት አወሳሰንም ለቅጣት ማክበጃነት ወይም ማቅለያነት ሊያገለግል ይችላል፡፡

አንቀጽ 42፡-የውሳኔ ሐሳብ ስለማቅረብ

ሀ. የዲስፕሊን ኮሚቴ የዲስፕሊን ጥፋቱን አጣርቶ እንዳጠናቀቀ ወዲያውኑ የምርመራውን ውጤትና ሊወሰድ የሚገባውን የዲስፕሊን እርምጃ የሚያመላክት የውሳኔ ሐሳብ ፊርሞ ተጠሪ ለሆነበት ኃላፊ ያቀርባል፤

ለ. የኮሚቴው የውሳኔ ሐሳብ የሚከተሉትን ሊይዝ ይገባል፤

- የተከሳሹን ሙሉ ስም፣ መታወቂያ ቁጥር፣ የሥራ/የትምህርት ክፍል፣ የትምህርት ዓመት፣ የሚኖርበት ሕንጻና ዶርም ቁጥር፣
- ተከሳሹ ተማሪ ከሆነ የተማሪውን የትምህርት ውጤት፣ የሠራኛ ከሆነ የሥራ አፈጻጸም
- የተከሳሹ የቀድሞ ሪከርድ
- የዲስፕሊን ጥፋቱን ዝርዝር፣ ደረጃና የተፈጸመበትን ሁኔታ
- የተከሳሽ ምላሽ
- የምስክሮችን ቃል፣
- ዝርዝር የውሳኔ ሐሳብ
- የኮሚቴው አባላት ፊርማ ያለበት ቃለ ጉባኤ ከነአባሪ ማስረጃዎች ጋር
- የሰብሳቢው ፊርማ ያለበት ሽኚ ደብዳቤ

ሐ. በዲስፕሊን ጥፋት የተከሰሰ ተከሳሽ ተጣርቶ ከተከሰሰበት ጉዳይ ነጻ መሆኑ ሲረጋገጥ ይህንኑ የሚገልጽ የጽሑፍ መረጃ ይሰጠዋል፡፡

አንቀጽ 43፡- የአስተዳደር ዘርፍ ም/ኃላፊ ውሳኔ

የተቋሙ ም/ኃለፊ ወይም የካምፓስ ኃላፊ የቀረበለትን የውሳኔ ሀሳብ በዚህ መመሪያ መሠረት ከመረመረ በኋላ ፡-

ሀ. የኮሚቴውን የውሳኔ ሐሳብ ሙሉ በሙሉ የማጽደቅ

ለ. ኮሚቴው ያቀረበውን የውሳኔ ሐሳብ የማሻሻል

ሐ. ኮሚቴው ጉዳዩን እንደገና እንዲመረምር ምክንያቶችን ገልጾ የማዘዝ ሥልጠን አለው፡፡

በተቋሙ ም/ኃላፊ ወይም በካምፓሱ ኃላፊ የጸደቀው የዲስፕሊን ውሳኔ ለተከሳሹ በጽሑፍ ይሰጠዋል፤ ከከባድ የጽሑፍ ማስጠንቀቂያ እና ከዚያ በላይ የዲስፕሊን እርምጃ የተወሰደበት ከሆነ ተመሳሳይ ቅጂ በዩኒቨርሲቲው ግቢ ውስጥ ባሉ የማስታወቂያ ሰሌዳዎች ላይ ይለጠፋል፡፡

አንቀጽ 44፡-የውሳኔ አፈጻጸም

ሀ. የዲስፕሊን እርምጃ ውሳኔ ከጸደቀበት ቀን አንስቶ ተፈጻሚ ይሆናል፡፡ ሆኖም ግን ተከሳሹ ከተቋሙ ግቢ የሚታገድ ከሆነ የ24 ሰዓታት ጊዜ ይሰጠዋል፡፡ ሆኖም እንደ አንድ ባለጉዳይ ከውጪ እየተመላለሰ መጨረስ ያለበት ጉዳይ ካለ የሚመለከተውን አካል አስፈቅዶ መጨረስ ይችላል፡፡

ለ. በንዑስ አንቀጽ (ሀ) ላይ የተጠቀሰው እንደተጠበቀ ሆኖ ጉዳዩን ይግባኝ ብሎ ይግባኙ ውሳኔ እስኪያገኝ ድረስ ለተቋሙ የበላይ ሃላፊ ጥያቄ አቅርቦ ከተፈቀደለት በግቢ ውስጥ ሆኖ እየተማረ/እየሠራ እና አገልግሎት እያገኘ ጉዳዩን መከታተል ይችላል፡፡

አንቀጽ 45፡- የዲሲፕሊን ጉዳይ ሰሚ ኮሚቴ የክስ አሰማም ሂደት (ስነ-ስርዓት)

1. ሰብሳቢው የኮሚቴውን ስብሰባ በሊቀመንበርነት ይመራል፡፡ ሰብሳቢው በማይኖርበት ጊዜ ምክትሉ ኃላፊነቱን ይረከባል፡፡
2. የኮሚቴውን ቃለ ጉባኤ ጸሐፊው ይይዛል፡፡
3. ተከሳሹ በጽሑፍና በቃል መልስ የማቅረብ መብት አለው፡፡
4. ከፍተኛና አሳማኝ በሆነ ምክንያት ተከሳሹ በክርክሩ ሂደት መሳተፍ ያልቻለ እንደሆነ ሲታመን እስከሚችልበት ቀን ድረስ ክርክሩ እንዲቆይ ሊደረግ ይችላል፡፡

5. ተከሳሹ ክሱን ለማስረዳት ከሳሽ ያቀረባቸውን ምስክሮች የመጠየቅ መብት አለው፡፡ ከሳሽም ተከሳሽ ያቀረባቸውን የመከላከያ ምስክሮች የመጠየቅ መብት አለው፡፡
6. ተከሳሹ ዝም የማለት መብት አለው፡፡ ነገር ግን ዝምታው አምኖ እንደመቀበል ይቆጠራል፣

ክፍል አስር
የቅጣት አወሳሰን

አንቀጽ 46፡- ቅጣት ስለማቅለል

ከዚህ ቀጥሎ የቀረቡት ምክንያቶች ለዲስፕሊን ጥፋቶች ለሚሰጡ ቅጣቶች የቅጣት ማቅለያ ሊሆኑ ይችላሉ፡፡

1. ጥፋተኛው ከዚህ በፊት መልካም ስነ ምግባር የነበረው መሆኑ ከመዝገብ ሲረጋገጥና ከዚህ በኋላ የመድገም ሀሳብ የሌለው እንደሆነ በመፀፀት በጽሑፍ ያቀረበ ከሆነ፣
2. ጥፋቱን የፈፀመው ከባድ አደጋ እየደረሰበት መስሎት ራሱን ለመከላከል በሚያደርገው ሙከራ ከሆነ፣
3. ጥፋቱን እንዲፈፀም የተገፋው እጅ ካለበት፣
4. ጥፋቱን ሲፈጽም አጥፊው በከፍተኛ አካላዊና ስነ-ልቦናዊ ጭንቀት ውስጥ ከነበረ፣
5. ጥፋተኛው የሚጠበቅበትን ሁሉ በማድረግና ጥፋቱን በማመን ከፍተኛ የመፀፀት አዝማሚያ ያንፀባረቀ እንደሆነ፣

አንቀጽ 47፡- ቅጣት ስለማክበድ

የዲስፕን ጥፋት በፈጸመ ተከሳሽ የሚተላለፍ የቅጣት ውሳኔ ላይ ቅጣቱን ሊያከብዱ የሚችሉ ጉዳዮች እንደሚከተለው ቀርበዋል፡፡

1. ተደጋጋሚ፣ በሌሊት ወይም ጨለማን ተገን በማድረግ፣ የጦር ወይም ሌላ አደገኛ መሳሪያ በመያዝ ከሆነ፣
2. ጥፋቱን የፈፀመው ከሌሎች የወንጀለኞች ቡድን ጋር በመሆን በተለይ በመሪ ተዋናይነትና አደራጅነት ከሆነ፣
3. ጥፋቱን የፈጸመው በቡድን በመሆን ጥፋቱ የከበደና በሌላው ላይ አስቦና ሆነ ብሎ ጉዳት ለማድረስ ከሆነ፣
4. ጥፋቱን የፈፀመው በማናለብኝነት፣ የተሰጠውን ወይም ያለበትን አደራ ወደ ጐን በመተው ሆን ብሎ ለማጥፋት አስቦ ከሆነ፣
5. ጥፋቱን የፈፀመው በከፍተኛ ጥላቻ በመነሳት ወይም ሆን ብሎ አስቦበት ከሆነ፣
6. ጥፋቱን የፈፀመው ለጥል ባልተዘጋጁና ባላሰቡ ንጹሀን ወይም በተቋሙ የበላይ ኃላፊዎች፣ መምህራን ወይም በአስተዳደር ሠራተኞች ላይ ከሆነ፣

አንቀጽ 48፡- የዲስፕሊን ጥፋቱ በሪከርድነት በተያዘበት ወቅት ሲደገም

1. ቀድሞ ውሳኔ የተሰጠበት የዲሲፕሊን ግድፈት አነስተኛ ግድፈት ሆኖ ውሰኔው የሚያበቃበት ጊዜ ሳይደርስ በተመሳሳይ ምድብ ውስጥ የሚገኝ የድስፕሊን ጥፋት ከተደገመ እስከ አንድ ወሰነ ትምህርት ከትምህርት ገበታ ያሳግዳል፡፡ የተደገመው ግድፈት አነስተኛ የዲስፕሊን ጥፋት ካልሆነ ግን በአዲስ መልኩ ይታያል፡፡
2. ቀድሞ ውሳኔ የተሰጠበት ጥፋት ቀላል ሆኖ በተመሳሳይ ምድብ ውስጥ የሚገኝ ጥፋት ወይም አነስተኛ ጥፋት ከተደገመ ከአንድ እስከ ሁለት ዓመት ከትምህርት ገበታ ያሳግዳል፡፡ የተደገመው ጥፋት መካከለኛ ወይም ከፍተኛ ከሆነ በጣም ከፍተኛ የዲስፕሊን ቅጣት የሚጣልበት ይሆናል፡፡
3. ቀድሞ ውሳኔ የተሰጠበት ጥፋት መካከለኛ ወይም ከፍተኛ ከሆነ የትኛውም ጥፋት ቢፈጽም ሙሉ በሙሉ የሚሰናበት ይሆናል፡፡

አንቀጽ 49፡- ተደራራቢ የዲሲፕሊን ጥፋት ሲፈፀም የቅጣት አወሳሰን

ተከሳሹ ሁለት ወይም ከዚያ በላይ ከተቋሙ የሚያሳግዱ የዲሲፕሊን ግድፈቶች በአንድ ጊዜ ወይም በመጀመሪያ ለፈፀመው ጥፋት ውሳኔ ከማግኘቱ በፊት ፈጽሞ ከተገኘ ለእያንዳንዱ ጥፋት ቅጣት ከተቀመጠ በኋላ የሁሉንም ቅጣት በመደመር ይወሰናል፡፡ የሁሉም ድምር ከሶስት ዓመት ከበለጠ ሙሉ በሙሉ ከተቋሙ የሚሰናበት ሆኖ አግባብ ባለው ህግም ተጠያቂ ይሆናል፡፡

አንቀጽ 50፡-ውሳኔን ስለማሳወቅና ተያያዥ ጉዳዮች አፈጻጸም

1. ከምክር (ከግሳፄ) በስተቀር ማንኛውም በተከሳሽ ላይ በዲስፕሊን ጥፋት የሚወሰድ እርምጃ ለተከሳሹ በጽሑፍ ሊሰጠው ይገባል፡፡
2. በተቋሙ ውስጥ በማንኛውም ደረጃ የሚወሰድ የዲስፕሊን ጥፋት እርምጃ ቢያንስ ለግቢ ደህንነትና ጥበቃ፣ ለሚመለከተው የትምህርት ክፍል ኃላፊ፣ ለሚመለከተው የሥራ ክፍል፣ ለተማሪዎች ጉዳይ ዳይሬክተር፣ ለአስተዳደር ዘርፍ ም/ኃላፊና ለተቋሙ የበላይ ኃላፊ በግልባጭ ማሳወቅ ይገባል፡፡ የተጠቀሱት አካላትም በአግባቡ አደራጅቶ ማስቀመጥ ይኖርባቸዋል፡፡
3. ለተቋሙ ማህበረሰብ በሙሉ በግልጽ በሚታይ የማስታወቂያ ሰሌዳ ላይ በመለጠፍ ሌላው እንዲማርበት ይደረጋል።
4. ተከሳሹ ባጠፋው ጥፋት በጊዜያዊነትም ይሁን ሙሉ በሙሉ ከተቋሙ በሚታገድበት ወቅት የታገደበት ምክንያት በጽሑፍ ይገለጽለታል፡፡ በወቅቱ ተከሳሹ በተቋሙ በግቢ ውስጥ ባለመገኘቱ ወይም አድራሻው ባለመታወቁ ወይም በሌላ ምክንያት በአካል ሳይገኝ በመቅረቱ የታገደበትን ውሳኔ ለራሱ መስጠት ካልተቻለ ውሳኔው በተቋሙ ማስታወቂያ ሰሌዳ ቢያንስ ለአምስት ተከታታይ ቀናት ተለጥፎ እንዲቆይ ይደረጋል፡፡
5. ተከሳሹ የተከሰሰበት የዲስፕሊን ጥፋት ሙሉ በሙሉ ከተቋሙ እንዲታገድና ተማሪ ከሆነ የትምህርት ማስረጃው እንዳይሰጠው ካልተወሰነበት በስተቀር እስከ ዕግዱ ያለው የትምህርት ማስረጃ በዲስፕሊን ጥፋት ምክንያት ያቋረጠ መሆኑን ከሚገልጽ ሽኚ ደብዳቤ ጋር ይሰጠዋል፡፡
6. የተከሳሹ በጊዜያዊነትም ይሁን ሙሉ በሙሉ ከተቋሙ መታገድ ከዕግዱ ጋር ያልተያያዙ መብቶችንና ግዴታዎቹን ተፈጻሚነት አያስቀርም፡፡
7. ውሳኔ ለመስጠትም ይሁን ውሳኔ ከተሰጠ በኋላ የሰው ሀብት ልማትና አስተዳደር ዳይሬክተር፣ የተማሪዎች አገልግሎት ዳይሬክተር እና የተማሪዎች ህብረት የውሣኔ መጓተት እንዳይፈጠር አፈፃፀሙን ይከታተላሉ፡፡

አንቀጽ 51፡- የዲስፕሊን ጥፋት ቅጣትን በሪከርድነት ስለመያዝ

ማንኛውም ተከሳሽ የዲሲፕሊን ጥፋት የቅጣት ውሳኔ ከተላለፈበት በኋላ በግል ፋይሉ ውስጥ ገብቶ በሪከርድነት ሊያዝበት የሚችለው

1. ለአነስተኛና ቀላል የዲስፕሊን ጥፋቶች ቅጣት ከተላለፈበት ቀን ጀምሮ ለአንድ ዓመት ብቻ የሚቆይ ሲሆን በተከሳሹ ማህደር ውስጥ ከአንድ ዓመት በላይ ተቀምጦ ቢገኝ ዋጋ አይኖረውም፡፡
2. ለመካከለኛ፣ ከፍተኛና በጣም ከፍተኛ የዲስፕሊን ጥፋቶች ውሳኔ ከተላለፈበት ቀን ጀምሮ ተከሳሹ ተማሪ ከሆነ በሰነድነት በተመራቂው ፋይል ውስጥ ሁሌም ይቀመጣል፡፡

ክፍል አስራ አንድ
የይግባኝ ስነ-ሥርዓት

የይግበኝ ውሳኔ አሠጣጥ ሂደቱ ከዲስፕሊን ጥፋት ክስ አመሠራረት እስከ ውሳኔ አፈጻጸም ድረስ ካለው ጋር ተመሳሳይ ሂደትን የሚከተል ነው፡፡

አንቀጽ 52፡- የይግባኝ ሰሚ ኮሚቴ ስለማቋቋም

የተቋሙ የበላይ ኃላፊ **የተቋሙ የቅሬታ** ሰሚ ኮሚቴ እንዲመረምረው ያደርጋል፡፡

አንቀጽ 53፡- ይግባኝ የማቅረብ መብት

ሀ. ጥፋተኝነት የተወሰነበት ተከሳሽ ቅሬታውን (ይግባኙን) ለይግባኝ ሰሚ ኮሚቴ እንዲቀርብለት ለተቋሙ የበላይ ኃላፊ ውሳኔው ከተገለጸበት ቀን ጀምሮ ባሉት አምስት የሥራ ቀናት ውስጥ በጽሁፍ ማመልከቻ የማቅረብ መብት አለው፡፡ የይግባኝ ማመልከቻውም የሚከተሉትን መያዝ አለበት፡፡

1. የይግባኝ አቅራቢ ስም፣ መታወቂያ ቁጥር፣ ጾታና እድሜ
2. የሚሰራበት ሥራ ክፍል፣ ተማሪ ከሆነ የሚማርበት ፋካሊቲ፣ ትምህርት ክፍልና የትምህርት ዓመት
3. የቅሬታው መንስኤ

4. ደጋፊ ማስረጃዎች /ካሉ/
5. አመልካች የሚሻው መፍትሄ
6. ቀንና ፊርማ

ለ. የተቋሙ የበላይ ኃላፊ በወቅቱ የቀረበውን ቅሬታ አይቶ መጣራት አለበት ብሎ ሲያምን የተጻፈውን ማመልከቻ ከአስፈላጊ መረጃ ጋር ለይግባኝ ሰሚ ኮሚቴ ሊመራው ይችላል።

ሐ. ይግባኝ ሰሚ ኮሚቴ በተቋሙ የበላይ ኃላፊ የተመራለትን ማስረጃዎች አግባብነት ካላቸው የተቋሙ ህጎች፣ መመሪያዎችና ደንቦች አንፃር በመመርመር በሶስት የሥራ ቀናት ውስጥ ቅጣቱን ሊያፀድቀው፣ ሊያሻሽለው ወይም ውድቅ እንዲሆን ወይም እንደገና በዲስፒሊን ኮሚቴ እንዲመረመር ወይም ለየት ያለ ቅጣት እንዲወሰን ከዚህ መመሪያ ጋር የተገናዘበ አማራጭ የውሳኔ ሃሳብ ለተቋሙ የበላይ ኃላፊ ሊያቀርብ ይችላል፡፡ በዚህ ላይ የተቋሙ የበላይ ኃላፊ ውሳኔ ይሰጣል፡፡

መ. ይግባኝ የሚቀርብባቸው ጉዳዮች መካከለኛና ከዚያ በላይ ምድብ ላይ ለሚገኙ የዲስፕሊን ጥፋቶች ላይ በተላለፈ ውሳኔ ላይ ነው፡፡

አንቀጽ 54፡ የይግባኝ መሠረቶች

1. በዲስፕሊን ኮሚቴ ታይቶ በአስተዳደር ዘርፍ ም/ኃላፊ በጸደቀ የዲስፕሊን እርምጃ ላይ ቅሬታ ሲኖር
2. አዲስ ማስረጃ ካልተገኘ በስተቀር ይግባኝ መሠረት የሚያደርገው የዲስፕሊን ኮሚቴ ባሰባሰባቸው ማስረጃዎችና በውሳኔ መዝገብ ላይ ብቻ ነው፡፡ አዲስ የክስ ጭብጥ በይግባኙ ላይ አይቀርብም፡፡
3. የይግባኝ ሰሚ ኮሚቴ ይግባኙን ማየት አግባብ ሆኖ ካገኘው፡

ሀ. የመጀመሪያ ክርክሩ ስነ-ስርዓቱን ጠብቆ ስለመካሄዱ፣

ለ. የተወሰነው ውሳኔ በቂ ማስረጃ ላይ የተመሰረተ ስለመሆኑ

ሐ. ቅጣቱ ተከሳሹ አጥፍቷል ለተባለው ጥፋት ተመጣጣኝ ስለመሆኑ

መ.ተከሳሹ በዋናው ክርክር ሂደት ወቅት ሊያገኘው ያልቻለውና ውሳኔ ማስቀየር የሚችል ማስረጃ ካቀረበ ኮሚቴው የቀረበውን ማስረጃ መርምሮ በሶስት ውስጥ የውሳኔ ሐሳቡን ከመሸኛ ደብዳቤ ጋር በማያያዝ ለተቋ የበላይ ኃላፊ በጽሑፍ ያቀርባል፡፡

አንቀጽ 55፡- የቅጣት አፈፃፀም

1. በተከሳሹ ላይ የተወሰነውን ውሳኔ በማስታወቂያ ከወጣበት ሰዓት ጀምሮ ውሳኔው በጥፋተኛው ላይ ተግባራዊ ይሆናል፣
2. ተከሳሹ የይግባኝ ማመልከቻ አቅርቦ ይግባኙ አግባብ መሆኑ ከታመነበትና ተከሳሹ ሂደቱን በተቋሙ ውስጥ ወይም ሥራ ላይ ሆኖ መከታተል ከፈለገ ግቢ ውስጥ ወይም ሥራ ላይ በመቆየቱ በራሱ፣ በተቋሙ ማህበረሰብና ንብረት ላይ የሚያመጣው አደጋ አለመኖሩ ከታመነበት የይግባኝ ስርዓቱን እስኪጨርስ ግቢ ውስጥ ወይም ሥራ ላይ እንዲቆይ በተቋሙ የበላይ ኃላፊ ሊፈቀድለት ይችላል።

አንቀጽ 56፡- የተቋሙ የበላይ ኃላፊ ስልጣንና ኃላፊነት

ሀ. በዲሲፕሊን ጥፋት የተከሰሰ ተከሳሽ ጉዳይ በውሳኔ ሂደት ላይ እያለ የተከሳሹ ግለሰብ ከተከሰሰበት የዲስፕሊን ጥፋት ክብደት አንፃር በተቋሙ ግቢ ውስጥ መኖር ወይ ሥራ ላይ መገኘት ለእርሱና ለሌሎች ጉዳዩ ለሚመለከታቸው አካላት መልካም አለመሆኑን በማንኛውም መንገድ የተቋሙ የበላይ ኃላፊ ሲያውቅ ጉድዩ ተጣርቶ ውሳኔ እስኪሰጥበት ድረስ ተጠርጣሪው ሰብዓዊ መብቱ በአግባቡ ተጠብቆለት፣ አስፈላጊውን አገልግሎት ከተቋሙ ማግኘት በሚችልበት መንገድ በአካባቢው ፖሊስ ቁጥጥር ስር የማድረግ ሥልጣንና ኃላፊነት ይኖረዋል፡፡

ለ. በዚህ መመሪያ መሠረት ከተቋሙ ሙሉ በሙሉ ለተሰናበቱ ተከሳሽ ግለሰቦች የተቋሙ የበላይ ኃላፊ ሁኔታዎችን ግምት ውስጥ አስግብቶ ይቅርታ የማድረግ ወይም ውሳኔውን የማሻሻል ሥልጣን አለው፡፡ ሆኖም ተከሳሹ ያጠፋው ንብረት ዋጋ ያለው ከሆነ ተተምኖ እንዲከፍል ማድረጉን አያስቀርም።

ሐ. የተቋሙ የበላይ ኃላፊ በዲስፕሊን ጥፋት ተከሶ የጥፋተኝነት ውሳኔ ከተላለፈ በኋላ ይቅርታ የሚያደርግለት ወይም ውሳኔውን የመገደብ ስልጣኑን የሚጠቀመው ተከሳሽ የቀድሞ ሪከርዱንና ከጥፋቱ ተምሮ የተፀፀተ መሆኑን ሲያረጋግጥና ይህንንም የሚገልጽ የይቅርታ ደብዳቤ በጽሑፍ ተከሳሹ ሲያቀርብና ሲታመንበት ነው።

አንቀጽ 57፡ የመጨረሻ ውሳኔ

በዲስፕሊን ጉዳይ የተቋሙ የበላይ ሃላፊ ውሳኔ የመጨረሻ ይሆናል፡፡

ክፍል አስራ ሁለት
ልዩ ልዩ ድንጋጌዎች

አንቀጽ 58፡- የሰዓት ገደብ

58.1. ማንኛውም ተማሪ ከምሽት 1፡00 ሰዓት ጀምሮ እስከ ንጋቱ 12፡30 ሰዓት ድረስ ከግቢ መውጣትም ሆነ ወደ ግቢ መግባት የተከለከለ ነው፡፡

58.2. ከተማሪ ውጭ ያሉ ሌሎች ግለሰቦች በልዩ ሁኔታ ከላይ ከተጠቀሰው ሰዓት ውጭ ወደ ግቢ መግባትና ከግቢ መውጣት ቢያስፈልግ ኃላፊነት በተሰጠው አካል ፈቃድ ማግኘት አለባቸው፡፡

አንቀጽ 59፡- ልዩ ፍላጎት ያላቸው ተማሪዎች፣ መምህራንና አስተዳደር ሠራኞተችን በሚመለከት

59.1. ከፍተኛ ትምህርት ተቋማት የአካል ጉዳት ያለባቸውና የሌሎችን ድጋፍ የሚሹ የከፍተኛ ትምህርት ማህበረሰብ አባላት ሲኖሩ እነርሱና የሚያግዙአቸው ሊያደርጉት ስለሚገባ ጥንቃቄ እንደየልዩ ፍላጎታቸው ዓይነትና መጠን ግንዛቤ መፍጠርና ስልጠና መስጠት አለባቸው፡፡

59.2. ልዩ የመማሪያ ክፍል፣ የቤተ መጽሐፍት፣ የምግብ አቅርቦት የሚፈልጉ ሆነው ሲገኙም አገልግሎቱን የሚያገኙበትን ልዩ ሁኔታ እንዲመቻችላቸው ይመከራል፡፡

59.3. ምንም ዓይነት ልዩ ፍላጎት ቢኖራቸውም ከሌሎች ሰዎችች ጋር ግቢ ውስጥ በሚሆኑበት ጊዜ ሁሉ አካላዊ ርቀትን የመጠበቅ፣ እጅ የመታጠብ፣ አፍና አፍንጫ መሸፈኛ ማስክ የመጠቀም ግዴታ አለባቸው፡፡

አንቀጽ 60፡- የዲስፕሊን ውሳኔና እርምጃ አወሳሰድ

ከኮቪድ -19 በሽታ ስርጭት ለመከላከልና ለመቆጣጠር የወጣውን ይህንን መመሪያ ጥሶ የተገኘ ማንኛውም የከፍተኛ ትምህር ተቋም ማህረሰብ አባል ቀደም ሲል የነበረውን የዲስፕሊን ውሳኔና እርምጃ አወሳሰድ ሂደት ሳይጠብቅ በልዩ ሁኔታ አፋጣኝ ውሳኔ የሚሰጥበትና እርምጃ የሚወሰድበት አሠራር በተቋሙ የበላይ ኃላፊ ውሳኔ ተግባራዊ ሊሆን ይችላል፡፡

አንቀጽ 61፡- ተፈፃሚነት ስለማይኖራቸው ህጐች

ከዚህ በፊት ሲሰራበት የነበረው የትምህርና ስልጠና የዲሲፕሊን መመሪያ በዚህ መመሪያ የተተካ በመሆኑ ተፈፃሚነት አይኖረውም፡፡ ዲስፕሊንን የሚመለከቱ ሌሎች ህጎችና ልማዳዊ አሠራሮች በዚህ መመሪያ በተጠቀሱ ጉዳዮች ላይ ተፈጻሚነት አይኖራቸውም፡፡

አንቀጽ 62፡- የመተባበር ግዴታ

ማንኛውም ሰው ወደ ግቢ ውስጥ ሲገባም ሆነ በግቢ ውስጥ በሚያደርጋቸው እቅስቃሴዎች ሁሉ ይህን መመሪያ የማክበርና የማስከበር ግዴታ አለበት፡፡

አንቀጽ 63፡- የማስፈጸም ኃላፊነት

ይህንን መመሪያ የተቋሙ የበላይ ኃላፊ ለማህበረሰብ በሙሉ የማስተዋወቅና ግንዛቤ በመፍጠር በበላይነት የማስፈጸም ኃላፊነት አለበት፡፡

አንቀጽ 64፡- ክትትል፣ ግምገማና ሪፖርት

የከፍተኛ ትምህርት ተቋማት በተቋማቱ ግቢ ውስጥ የዚህን መመሪያ አተገባበር ሂደትንና ውጤቱን የመከታተል፣ የመገምገምና በመደበኛነት ለሳይንስና ከፍተኛ ትምህርት ሚኒስቴር ሪፖርት የማቅረብ ኃላፊነት አለባቸው፡፡

አንቀጽ 65፡- *መመሪያውን ስለማሻሻልና ስለመሻር*

ይህ መመሪያ አስፈላጊ ሆኖ ሲገኝ የሳይንስና ከፍተኛ ትምህርት ሚኒስቴር ሊያሻሽለው ወይም ሊሽረው ይችላል፡፡

አንቀጽ 66፡- *መመሪያው የሚጸናበት ጊዜ*

ይህ መመሪያ ከመስከረም 30 ቀን 2013 ዓ.ም ጀምሮ የጸና ይሆናል፡፡

……

ሳሙኤል ኡርቃቶ (ዶ/ር)

የሳይንስና ከፍተኛ ትምህርት ሚኒስቴር

ሚኒስትር